# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 305 ሐምሌ 5 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ፡- ከፋ ደሳል

አቶ ኡመር ሁሴን

## እስከአሁን 2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ችግኞች መተከላቸው ተገለጸ

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ ፡- እስከ አሁን በተሰራው ሥራ 2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ችግኝ መተከላቸውን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ ፡፡ አረንጓዴ አሻራ አየር ንብረት ለውጥን ከመከላከል በተጨማሪ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ጉልህ ሚና እንዳለው ተገልጿል፡፡

የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ኡመር ሁሴን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ለዘንድሮ አረንጓዴ አሻራ ተከላ ከተዘጋጁ 7 ነጥብ 6 ቢሊዮን ችግኞች እስካሁን ድረስ በተሰሩ ሥራዎች 2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ችግኞች መተከላቸውን ጠቁመው፤ የቀረው በቀሪው ወራት ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ገልጸዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ አረንጓዴ አሻራ በዋናነት አየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል ጉልህ ሚና ከማበርከቱም ባሻገር በግብርናው ዘርፍ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

እስከአሁን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## አረንጓዴ አሻራው ስነምህዳሩን በመጠበቅ ረገድ ውጤት እያመጣ መሆኑ ተገለጸ

ጌትነት ተስፋማርያም



ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

አዲስ አበባ፡- የአካባቢን ስነምህዳር ለመጠበቅ የሚደረገው ጥረት አበረታች መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ሠራተኞች አስታወቁ። የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ሠራተኞች በጉለሌ የዕጽዋት ማዕከል ትናንትና የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር አከናውነዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ኃላፊና የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር ኃላፊ ተፈሪ ፍቅሬ፤ ባለፉት ሶስት ዓመታት የተተከሉ ችግኞች በስነምህዳር ጥበቃው ላይ በጎ ውጤት ማሳየታቸውን ገልጸዋል።

በየአካባቢው የሚተከሉ ችግኞች ለአካባቢ ጥበቃ ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ ታይቷል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ዕርጥበትን በመጨመርና የተፈጥሮ ሃብትን በመጠበቅ ረገድ ካለፉት ዓመታት የተሻለ ውጤት እያስገኙ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደአገር የአካባቢ ጥበቃ ባህሉም እየዳበረ መጥቷል። አሁን ላይ መትከሉ ብቻ ሳይሆን የተከሉትን ችግኝ መንከባከቡም እየተለመደ ነው። በቀጣይም የተፈጥሮ ሃብቱን ለሚመጣው ትውልድ ጠብቆ ለማቆየት የተቀናጀ የችግኝ ተከላና እንክብካቤ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የአገልግሎቶችና መልካም አስተዳደር ክትትል ሚኒስትር ዴኤታ ዓለምፀሐይ ጳውሎስ በበኩላቸው ፤ ለትውልድ በምናሳርፈው አሻራ እንደአገር ስነምህዳሩን የሚጠብቅ ሥራ መከናወኑ አበረታች ነው ብለዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ሰራተኞችም የአካባቢ ጥበቃ ሥራውን ለማገዝ እያንዳንዳቸው አየር ብክለትን ለመከላከል የሚረዱ 25 አገር በቀል ችግኞችን መትከላቸውን ገልጸው፤ ሠራተኞቹ በቀጣይ በነፍስ ወከፍ እስከ 100 ችግኞችን እንዲተክሉ ይደረጋል ሲሉ ጠቁመዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤትም የአረንጓዴ

አረንጓዴ አሻራው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

pepsi

አርሾ ሜዲካል ላቦራቶሪ ኃ.የተ.የግ.ማ
ARSHO MEDICAL LABORATORIES P.L.C
በትውልድ የታመነ!
አድራሻ - አራት ኪሎ፣
ከአራዳ ክፍለ ከተማ ሕንፃ ጀርባ፣
የ24 ሰዓት አገልግሎት
612
0114-16-70-89
0911-10-18-18




ፎቶ፡- ከፋ ደሳል

## “መንግሥት የአገርን ሰላም ለማስጠበቅ እያደረገ ያለው ጥረት በጎ ጎን ቢኖረውም በቂ አይደለም”

\- ዶክተር ራሔል ባፌ
የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- መንግሥት የአገርን ሰላም ለማስጠበቅ እያደረገ ያለው ጥረት በጎ ጎን ቢኖረውም በቂ ባለመሆኑ

“መንግሥት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

UNIC ETHIOPIA
ሕብረት ኢንሹራንስ አማ
THE UNITED INSURANCE COMPANY SC
Tomorrows Company Today
+251 111 26 34 34
united.insurance@unic-ethiopia.com
7469
ለህይወት
ሁሉም የመድን ፍላጎትዎ
ህጋዊ ግዴታዎ
ለንብረት

# “ኢትዮጵያ ላይ እየተካሄደ ያለው የግራጫ ጦርነት ነው”

- ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

**ዘላለም ግዛው**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ላይ እየተካሄደ ያለው ነጭ መዝገብ ወይም ጥቁር መዝገብ ላይ የተቀመጠ ሳይሆን የግራጫ ጦርነት ባሕሪ ያለው  ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ።

ባለፈው ሐሙስ በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 16ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ የሰጡት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንደገለጹት፤ አንደኛው ጦርነት የመረጃ ጦርነት ነው ብለዋል።

በዚህ የመረጃ ጦርነት  በአንድ ቀበሌ ውስጥ የሚፈጸም ሞት ብዙ የዓለም ተዋናዮች በአንድ ጊዜ እንዲያውቁት ይደረጋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህ የመረጃ ጦርነት በስንዴ ወይንም በአረንጓዴ አሻራ ላይ ኢትዮጵያ አስደማሚ ሥራ ስትሰራ አይገኝም ብለዋል።

የግራጫ ጦርነቱ አንድ አካል የሆነው የመረጃ ጦርነት የተቀናጀ ስለሆነ ለማቆም ብዙ ሙከራዎችን ብናደርግም ቀላል አይደለም ብለዋል።

ሁለተኛው የዲፕሎማሲ ጦርነት መሆኑን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ባደጉ አገራት በየደቂቃው ግድያ አለ፤ በየቀኑ ሰው ይሞትባቸዋል፤ እዛ ግን የከተማው ሚዲያ ከሚያወራው ውጭ አጀንዳ ስለማይሆን፣ መረጃው ለእኛም አይደርስም ብለዋል። በከተማቸው ሰው እየተገደለ፣ ልጆቻቸው እየሞቱ ያንን መከላከል ሳይችሉ የኢትዮጵያ ጉዳይ ግን አስጨንቋቸው የዓለም አጀንዳ ማድረግ ይፈልጋሉ ሲሉ ተናግረዋል።

ሌላው የተልእኮ ውጊያ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እግርና ጭንቅላት አልባ ተላላኪ ባንዳዎችን ጨው እያቀመሱ ይልኳቸዋል፤ እነዚህ እግር አልባ ባንዳዎች ሳይቸገሩ የራሳቸውን ዜጋ፣ የራሳቸውን ቤተሰብ ለመግደል ይፍጨረጨራሉ  ብለዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ያለውን በጋራ የመኖርና አገር የማጽናት ፍላጎት ለማፍረስ የተመረጡ አካባቢዎች አሉ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከነዚህም ውስጥ ኦሮሞና አማራን ፣ አማራን እርስ በእርሱ ፣ ኦሮሞን እርስ በእርሱ፤ አፋርና ሱማሌን፣ ሲዳማና ወላይታን፣ ቤኒሻንጉልን ከአማራ ወይም ከኦሮሚያ ጋር ማፋጀት የተመረጡ ስልቶች ናቸው ሲሉ ጠቅሰዋል። ከዛም ሲያልፍ ሙስሊም እርስ በእርሱ፤ ክርስቲያንም እርስ በእርሱ እንዲፋጅ ማድረግም ይስተዋላል ብለዋል።

በዚህ ሂደት እስካሁን ኢትዮጵያን ለማፍረስ አልተቻለም። በብዙ አገራት ያለው ልምምድ እነዚህ ካልተሳኩ ሰበብ ፈጥሮ ጦር ማዝመት ነው። ይሄ የመጨረሻ ግብ አይደለም። በሚዲያ ካፈረስክ መልካም፣ ያ ካልሆነ በዲፕሎማሲ ጫና ማፍረስ፣ ይህ ካልተሳካ በተልእኮ ጦርነት ማፍረስ፣ ይሄ የማይሳካ ከሆነ ግን ገብቶ ማፍረስ ነው አላማቸው ሲሉም ተናግረዋል።

“ለምክር ቤቱ ለማረጋገጥ የምፈልገው  መግደል ይችላል፣ ማጋደል ይችላል፣ በኢኮኖሚ ጫና ማዳከም ይችላል፤ ይሄንንም ሲያደርጉት ቆይተዋል፣ ነገር ግን ማንም አገር ከኢትዮጵያ ጋር ተዋግቶ  ማሸነፍም፣ ኢትዮጵያን ማፍረስም አይችልም” ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ በሩ ብዙ ነው፤ ዛሬ በሰሜን፣ ነገ በምስራቅ፣ ከእዛ በደቡብ በየቀኑ የሚያዳክሙበትና ሥራ የሚያስፈቱበትን ነገር ይፈጥራሉ ሲሉም ጫናውን አስረድተዋል።

በሌላ በኩል አገራቸው በብዙ ነገር ስትደበደብ፣ በብዙ ነገር ስትወቀጥ የት እንደነበሩ የማናውቃቸው ሁሉ ግድያ ሲኖር፣ ወረራ ሲደረግ፣ ጫና ሲካሄድ ይነግዱበታል ብለዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ ባንዳው ሸኔ ብቻ አይደለም። አዲስ አበባም ባንዳ አለ። እንደዚህ አይነት ሽቃይ ስብስብ በሚኖርበት ሰዓት የሚያጠቁን ኃይሎች የተሻለ ጉልበት ያገኛሉ። ይህንን ግራ መለስ ፈተናና የግራጫ ጦርነት ቀድመን ስለተገነዘብን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያስፈልገው የህግ ተቋማትን ማጠናከር መሆኑን ተገንዝበናል ብለዋል።

የፀጥታ ኃይሉን ስናዋቅርም አራት ነገሮች መርህ እንዲሆኑ አድርገን መፍጠር አለብን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በነዚህ ተቋማት ውስጥ የሚገባ የዘር ፣ የእምነት እና የፖለቲካ አመለካከት ይዞ እንዳይገባ እንዲሁም በትጥቅም ተታልሎ የአገርን አንድነት አደጋ ውስጥ የሚያስገባ መሆን እንደሌለበት በማመን መሆን አለበት ሲሉ አጽንኦት ሰጥተዋል። ይህም በሪፎርሙ ተግባራዊ መደረጉን አብራርተዋል።

ዛሬ ያለው የመከላከያ ኃይል በፊት ከነበረው አንጻር በእጅጉ የተሻለ ነው። በደህንነት ተቋማት ከፍተኛ የሆነ የተቋም ግንባታ ሥራ እየተሰራ ነው። በዚህ ሂደት መከላከያ ቢያንስ 95 በመቶ ተሳክቶለታል፤ ወደ 100 በመቶ ማደግ አለበት። ፖሊስና ደህንነትም በብዙ አድጓል ሲሉም የሪፎርሙን ስኬታማነት ጠቅሰዋል።

አንድ ቦታ ችግር ሲፈጠር እሱን ይዞ ሃገር እንደፈረሰ አድርጎ የማቅረብ ሁኔታ እንደሚታይ የገለፁት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለዚህም የጥምቀት በዓልን እንደምሳሌ አንስተዋል።

የጥምቀት በዓል በኢትዮጵያ ደረጃ 22 ሺህ ቦታ ሲከበር ታቦት በሰላም ወጥቶ በሰላም ገብቷል፤ ከዚህ ውስጥ ግን የሚዲያው ትኩረት የነበረው በወይብላ ማርያም የነበረው ችግር ነበር ብለዋል። በተመሳሳይ ያለፈው የረመዳን ኢድ በኦሮሚያ ብቻ ከስምንት ሺህ 800 በላይ ቦታ ላይ የጁምአ ሰላት በሰላም ተሰግዷል፤ ነገር ግን መስቀል አደባባይ ላይ የነበረው ችግር እንዲጎላ ተሰርቷል። እነዚህ ክፍተቶች እንዳይፈጠሩ መስራት እንዳለብን እናምናለን። ነገር ግን ከዚህ በስተጀርባ ያለው የግራጫ ጦርነት ነው ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳብራሩት፤ የሰራዊት አባላት ያንን ለማስታገስ ይሮጣሉ። አልፎ አልፎ ደግሞ አሳዛኝ ነገር ይፈጠራል። በዚህ ጊዜ ከምክር ቤት አባላትና ከኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠበቀው ጠላትን መለየት ወገን መሰብሰብ ነው። ኮሽ ባለ ቁጥር እርስ በእርስ መጠራጠር ከጀመርን ለጠላት ምቹ ሁኔታ እንፈጥራለን ብለዋል።

በመሆኑም ይህንን የግራጫ ጦርነት ለማሸነፍ መተባበር ብቸኛው መፍትሄ እንደሆነ አጽንኦት ሰጥተዋል።

# አገልግሎቱ 50 ልዩ አገር አቋራጭ አውቶብሶችን ተረከበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፐብሊክ ሰርቪስ አገልግሎት የቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ያመረታቸውን 50 ልዩ ሀገር አቋራጭ አውቶብሶች ተረከበ።

በርክክብ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስትሯ ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስን ጨምሮ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ በዚሁ ጊዜ እንደተናገሩት፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዘመናዊ አሰራር የተከተለ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም የቴክኖሎጂ መረብ በመጠቀምም የኤሌክትሮኒክስ ቲኬት አገልግሎት መስጠት ጀምረናል ብለዋል፡፡

አውቶብሶቹ ከፍተኛ የፈረስ ጉልበት ያላቸውና የ45 ሰዎች መቀመጫ፣ በቂ የሆነ የእቃ መጫኛ ፣ በውስጡም የመጸዳጃ እና የማቀዝቀዣ ክፍል ያላቸው ሲሆኑ ሙሉ በሙሉ አርቴፊሻል ኢንተለጀንት ሲስተም የተገጠመላቸውና ቅንጡ መሆናቸው በቁልፍ ርክክብ ሥነሥርዓቱ ላይ ተገልጿል። ርክክብ የተደረገባቸው አውቶብሶች የማህበረሰቡን የትራንስፖርት ችግር በመቅረፍ በኩል ያላቸው ሚና የጎላ መሆኑም ተመላክቷል።

# የአረፋን እሴት የዘወትር እናድርገው

**በሃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የኢድ አል አድሃ በዓል በመደጋገፍ እና በመረዳዳት ላይ የተመሰረተ መሆኑን የኋላው ታሪካችን ያሳያል ሲሉ የአዲስ አበባ የእስልምና ምክር ቤት የቦርድ ጸሐፊ አቶ ቶፊክ መሀመድ ተናገሩ።

በዓሉ ሸሪኣው በሚያዘው መሰረት  ከአላህ ትልቅ ምንዳ የሚገኝበት በመሆኑ ምስኪኖችን መደገፍ የዘወትር ተሳትፎ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

በዓሉ አንዱ ጠግቦ እያደረ ሌላው ጾሙን ማደር እንደሌለበት ያስተምራል ያሉት አቶ ቶፊቅ፤ ይህ ደግሞ በምግብ ብቻ ሳይሆን በአልባሳትና በገንዘብ ጭምር መሆን እንደሚገባ አመላክተዋል።

በበዓል ወቅት ይህ እሴት በብዙ ሰዎች ዘንድ ይተገበራል ያሉት አቶ ቶፊቅ፤ ሆኖም ይህ እሴት በበዓል ብቻ ተወስኖ ሳይቀር የዘወትር ቢሆን ችግረኞችን በመርዳት ድህነትን ማጥፋት ይቻላል ብለዋል።

አቶ አብዲ ከማል በበኩላቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት  አረፋ በዓል ያለህን በመካፈል ከጎረቤት ጋር በመጋራት የሚከበር በዓል ነው።

ሀዲስ ላይ በግ እንኳን ከተገዛ ለክርስትና እምነት ተከታዮች እንዳይሸታቸው ከተቻለ ገዝቶ መስጠት፤ እንደሚገባ ካልተቻለ ደግሞ  አብሮ መብላት እንደሚገባ ያስቀምጣል ብለዋል።

በመሆኑም ይህንን በጎ እሴት ሁል ጊዜ በሕይወታችን የእለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ተግባራዊ ብናደርገው መልካም ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በሥራ ምክንያት ኑሯቸውን በአዲስ አበባ ያደረጉት አብዛኛዎቹ የእምነቱ ተከታዮች ከቤተሰባቸው ጋር ወደ ክፍለሀገር በመሄድ በመደጋገፍ ያከብራሉ ያሉ ሲሆን



አቶ ቶፊክ መሀመድ



ሀይረዲን ኬዲር

በዓሉ የመረዳዳት እና ለተቸገሩ የሚረዳበት በዓል መሆኑንም አመላክተዋል።

አቶ ሀይረዲን ከድር በበኩላቸው እንደገለጹት፤ አብሮ መብላት እና አብሮ መደሰት የበዓሉ መገለጫ ሲሆን ሃይማኖታዊ ትዕዛዝ ያለው ነው። አንድ በሬ ለሁለት ለአራት ቢገዛ አንዱ እጅ ወይም መደብ ለምስኪኖች የሚቀመጥበት እና አቅም ለሌላቸው የሚታደልበት ሁኔታ አለ። ይህ ደግሞ ከሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን ከማህበራዊ ሕይወት አንጻርም መልካም አብሮነትን የሚፈጥር ነው። በመሆኑም ይህ እሴት የሁል ጊዜ እንዲሆን መስራት ይገባናል ብለዋል።

በተጨማሪም የታመመን መጠየቅ የተቸገረን ማጽናናት፣ በአልባሳት መደገፍ ከበዓሉ መገለጫ ባህሪዎች መካከል ነው ብለዋል።

# ”ገለልተኛ የሆነ ዘላቂ የዴሞክራሲ ተቋም የመገንባት ጉዳይ አንገብጋቢ ነው“

## - አቶ ታገሰ ጫፎ
## የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ

አዲስ አበባ፡- ገለልተኛ የሆነ ዘላቂ የዴሞክራሲ ተቋም የመገንባት ጉዳይ አንገብጋቢ መሆኑን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሠ ጫፎ ገለጹ።

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሠ ጫፎ ምክር ቤቱ ያዘጋጀው የዴሞክራሲ ተቋማት በሆኑት የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተርና የመገናኛ ብዙኃን የማሻሻያ የለውጥ ሥራዎችን የተመለከተ የምክክር መድረክ ትናንት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ገለልተኛ የሆነ ዘላቂ የዴሞክራሲ ተቋም የመገንባት ጉዳይ አንገብጋቢ ነው። ተቋማቱን በአሠራር፣ በሠው ኃይልና በቴክኖሎጂ መገንባት ትኩረት ያስፈልጋል።

ምክር ቤቱ በተቋማቱ የቀረቡለትን ሪፖርቶችና ተቋማት ያሳለፉትን ህጋዊ ውሳኔ የማስፈፀም፣ የማጣራትና ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለበት አመልክተው፤ግንዛቤ ማስጨበጥና ማስተማር ትኩረት እንደሚሰጠውና ይህም የተቋማቱን እንቅስቃሴ ከማሳወቅ ባለፈ የህዝቡን ጥያቄ ለመመለስ ያስችላል ብለዋል።

በተለይም መገናኛ ብዙሃን ትክክለኛና ሚዛናዊ መረጃ ለህብረተሰቡ እንዲደርስ በትጋት መስራት እንዳለባቸው ገልጸው፤ ምክር ቤቱም ክትትሉን ያጠናክራል ነው ያሉት።

በተጀመረው የ2015 በጀት ዓመት በጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ላይ ጠንካራ ቁጥጥር እንደሚደረግ ያመለከቱት አፈ-ጉባኤው፤ ይህም የዴሞክራሲ ስርዓትን በሕግ ስርዓት ውስጥ ለመገንባት ያስችላል ብለዋል።

የዴሞክራሲ ስርዓትን በሕግ ስርዓት ውስጥ ለመገንባት በጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ላይ ጠንካራ ቁጥጥር እንደሚደረግ ተናግረዋል።



የዴሞክራሲ ተቋማት አደረጃጀትና የማሻሻያ ጉዳዮች ህግን ጠብቀው የሚሰሩበት መንገድ መጠናከር እንዳለበትም ገልጸዋል።

በመድረኩ ላይ ያከናወኗቸውን የለውጥ ሥራዎች ያቀረቡት የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በሠው ኃይልና በአደረጃጀት ረገድ የተለያዩ ሥራዎች መስራታቸውን ገልጸዋል።

በተለይም የሕግ ማዕቀፎችን በማሻሻል፣ የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋትና ባለሙያዎችን በሙያ በማደራጀት የለውጥ ሥራዎች መከናወናቸውን ጠቅሰዋል።

በዚህም ተቋማቱ ቀደም ሲል ከነበረው የላቀ ስኬት እንዳስመዘገቡ ጠቅሰው፤ የአስፈጻሚ አካላት ገለልተኛ አለመሆንና የቁጥጥር ማነስ ተግዳሮቶች እንደነበሩ አንስተዋል።

“ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን፤ ጠንካራ፣ የተረጋጋች ሰላማዊ ሀገር የመገንባት ጉዳይ ነው” ያሉት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ አቶ ተስፋዬ በልጅጌ፤የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ የዴሞክራሲ ባሕል ግንባታ ሥራ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ተስፋዬ ገለጻ፤ ገለልተኛ የዴሞክራሲ ተቋማትን ለመገንባት የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ። ኢትዮጵያዊ የሆኑ ጠንካራ ተቋማትን ለመገንባት የሁሉም ባለድርሻ አካላት ትኩረት ወሳኝ ነው። ለአብነትም በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና በዕንባ ጠባቂ ተቋም በኩል ለውጥ ለማምጣት ታልመው የተከናወኑት ሥራዎች አበረታች ናቸው።

በመድረኩ ላይ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተር፣ የመገናኛ ብዙኃንና የተለያዩ ተቋማት ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

# ክልሉ ለትምህርት ቀዳሚ ትኩረት በመስጠት ሁለንተናዊ እድገት ለማስመዝገብ እየሰራ መሆኑ ተገለጸ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አገሪቱን ከገባችበት ችግር ለማውጣት ብሎም ሁለንተናዊ እድገት ለማረጋገጥ ለትምህርት ቀዳሚ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ርዕሰ መስተዳድሩ ተናገሩ፡፡

ሰሞኑን የአምቦ ኢፋ ቦሩ 2ኛ ደረጃ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት በተመረቀበት ወቅት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ እንደተናገሩት፣ ክልሉ የትምህርት ተደራሽነት ጥራትን ለማጣጣም በልዩ ትኩረት እየሰራ ይገኛል፡፡

ከዚህ አንጻር ክልሉ በአንድ ዓመት ውስጥ ከ100 በላይ የኢፋ ቦሩ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችና ሰባት የኢፋ ቦሩ 2ኛ ደረጃ ልዩ አዳሪ ት/ቤቶችን ገንብቷል ያሉት አቶ ሽመልስ፤ በዚህ ክረምት 6ሺህ ኢፋ ቦሩ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት አቅዶ አሁን ላይ የ1 ሺህ 200 ት/ቤቶች ግንባታ ተጀምሯል ብለዋል፡፡

ክልሉ ለትምህርት ተደራሽነት ት/ቤቶችን ከመገንባት ጎን ለጎን ለትምህርት ጥራት ልዩ ትኩረት በመስጠት በተለይ ኢፋ ቦሩ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በእውቀታቸውና በውጤታቸው ተመልምለው የመግቢያ ፈተና እንደሚወስዱ የጠቆሙት አቶ ሽመልስ፣ ትምህርት ቤቶቹ ለየት ባለ መልኩ ሰፊ ቦታ ላይ ከመገንባታቸው በተጨማሪ ደረጃቸውን የጠበቁ የሳይንስ፣ የውጭ ቋንቋዎች ቤተ ሙከራዎችና ከየትኛውም የዓለም አገራት በቪዲዮ ትምህርታዊ ገለጻዎች መከታተል የሚያስችሉ ስማርት ክፍሎች እንደተገጠመላቸውም ተናግረዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ እንደገለጹት፣ ትውልድ እንዲታነጽና አገር እንዲገነባ ለትምህርት በተለይ ለትምህርት ጥራት ልዩ ትኩረት መስጠት ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን አስገንዝበው፣ በዚህ ረገድ ኦሮሚያ ክልል ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት የሚደነቅና የሚደገፍ መሆኑንና ሌሎች ክልሎችም ተሞክሮውን በመውሰድ እንዲሰሩና ሚኒስቴሩም አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ አመልክተዋል፡፡

ካለመደማመጥ ጊዜ ብቻ ሳይሆን አገርም ሊያመልጠን ይችላል ያሉት ዶክተር ሳሙኤል፣የሚደማመጥና ከአገሩ አልፎ ለአህጉሩ መፍትሄ የሚሆን ዜጋ ለማፍራት የሚኒስቴሩ ሥራ እንዳለ ሆኖ ሁሉም የራሱን ሚና እንዲጫወት ጠይቀዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ በትምህርት ዙሪያ በተደረገው ጥናት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ፊደል መቁጠርና መጻፍ የማይችል ዜጋ በስፋት መኖሩ መረጋገጡ የሚያሳስብ ጉዳይ መሆኑን የተናገሩት ደግሞ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ ናቸው፡፡ እንደ ዶክተር ቶላ ማብራሪያ፣አምባገነናዊ የወያኔ ሥርዓትን ለማስወገድ የቁቤ ትውልድ ላይ ብዙ ሥራ ተሰርቶ ተሳክቷል፡፡ አሁንም ደግሞ በስነ ምግርና በእውቀት የታነጹ የነገ የአገሪቱ ብርሃን የሚሆኑ የኢፋ ቦሩ ትውልድ ለማፍራት ብዙ ት/ቤቶችን ከመገንባት በተጨማሪ በትምህርት ጥራት ላይም አበረታች ውጤቶች ተመዝግቧል፡፡ አሁንም የክልሉ መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ በቴክኖሎጂ እውቀት የተካነና በፈጠራ ችሎታው የተመሰከረለት ዜጋ ለማፍራት ትምህርት ላይ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሰሩ ነው፡፡

በእለቱ የክብር እንግዳ የሆኑት የኢትዮጵያ አየር ኃይል አዛዥ ሌተናል ጀነራል ይልማ መርዳሳ በበኩላቸው እንደተናገሩት፣ የኦሮሞ ህዝብ ለውጡን ለማምጣት ያደረገው መስዋእትነት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል፡፡ አሁን የሚያስፈልገን ግን በምግባርና በእውቀት ጀግና መሆን ነው፡፡

አገራችን ከድህነት ለመላቀቅ የምታደርገውን ጥረት ለማደናቀፍ ጠላቶች ከፍተኛ ርብርብ ላይ መሆናቸው ግልጽ ነው ያሉት ሌተናል ጄኔራል ይልማ፤ ነገር ግን የታቀዱ የልማት ሥራዎች ያለምንም ጥርጣሬ ከግብ እንደሚደርሱ ያላቸውን እምነት ገልጸዋል፡፡

# በዘጠኝ ወራት 800 እናቶች በወሊድ ምክንያት ሕይወታቸው አልፏል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት ዓመት በተደረገ የእናቶች ሞት ኦዲት በዘጠኝ ወራት ውስጥ 800 እናቶች በወሊድ ምክንያት መሞታቸውን የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ገለፀ። በተጠቀሱት ወራት በወሊድ ምክንያት ከሞቱት እናቶች መካከል 52 በመቶ ያህሉ ከ25 እስከ 34 የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ናቸው።



**ዶክተር መሳይ ሃይሉ**

የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መሳይ ሃይሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በ2014 በጀት ዓመት በተደረገ የእናቶች ሞት ኦዲት በዘጠኝ ወራት ውስጥ ብቻ 800 እናቶች በወሊድ ምክንያት ሞተዋል። በወሊድ ምክንያት ሕይወታቸውን ካጡ እናቶች መካከልም ወደ 66 በመቶ የሚጠጉት በገጠር አካባቢ የሚኖሩ እና የትምህርት ደረጃቸው ሲታይም አነስተኛ የትምህርት ዝግጅት የነበራቸው ናቸው።

የእናቶች ሞት ኦዲት ማለት በእርግዝና እና በወሊድ በእናቶች ላይ የሚከሰት ሞትን አስመልክቶ ክትትል የሚደረግበት የቅኝትና የዳሰሳ ሥራዎችን የሚያጠቃልል ሥራ ነው።

የእናቶች ሞት የተከሰተው በጤና ተቋማት ውስጥና ከጤና ተቋማት ውጭ ነው ያሉት ዶክተር መሳይ፤ ወደ 11 ነጥብ 4 በመቶ የሚሆነው የእናቶች ሞት የተከሰተው ከህክምና ተቋማት ውጪ በሚደረግ በቤት ውስጥ ወሊድ ነው። የተቀሩት እናቶች ደግሞ በጤና ተቋማት ውስጥ በወሊድ ምክንያት ሕይወታቸው አልፏል።

በተጨማሪም በወሊድ ጊዜ የሚከሰቱ ችግሮች የተወሳሰቡ ሊሆኑ እንደሚችሉ ካለመረዳት ወደ 41 በመቶ በወሊድ ወቅት የእናቶች ሞት እንደሚከሰት በእናቶች ሞት ኦዲት መለየቱን ዋና ዳይሬክተሩ አክለው ገልፀዋል።

እንደ ዶክተር መሳይ ገለፃ፤ አብዛኞቹ በወሊድ ምክንያት የሞቱ እናቶች ለሞት የተዳረጉት ከወሊድ በኋላ በሚያጋጥም ከፍተኛ የደም መፍሰስ እና በእርግዝና ምክንያት በሚከሰት የደም ግፊት ምክንያት ነው። እነዚህ ክስተቶች ፈጣን አገልግሎት በመስጠት ማዳን የሚቻሉ በመሆናቸው ለወደፊቱ እነዚህ ላይ አጠናክሮ መሥራት ያስፈልጋል።

ዋና ዳይሬክተሩ ለእናቶች ሞት ዋና ዋና ምክንያቶች የሚባሉት እንደተለዩ ገልፀዋል። ብዙ ጊዜ ከእርግዝና ጋር የተያያዙ ችግሮች ሲከሰቱ ቶሎ በመለየት ተገቢውን የጤና ክብካቤ በወቅቱ አለማግኘት፤ ወደ ሕክምና ተቋማት ዘግይቶና ችግሩ ከተወሳሰበ በኋላ መምጣት፤ ወደ ጤና ተቋማት ለመድረስ የመሰረተ ልማቶች አለመሟላት እና የጤና ተቋማት የቅብብሎሽ ሰንሰለት ደካማ መሆን የችግሩ ዋና ምክንያቶች በመሆን መለየታቸውን ተናግረዋል።

በእናቶች ሞት ኦዲት ላይ የተሠራው ሥራ ችግሩን ለመቅረፍ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ለመለየት ያስችላል ያሉት ዶክተር መሳይ፤ ቁጥሩ ቀላል የሚባል ስላልሆነ ምላሽ ለመስጠት የ10 ዓመቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ ጨምሮ በተለያየ መልኩ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ከዚህ በፊት የጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት ላይ ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በጤና ኬላዎችም ተገቢው የእርግዝና ክትትል እንዲደረግ ይሠራል። ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ሲያጋጥሙም ወደ ጤና ጣቢያ ሪፈር እንዲያደርጉ የቅብብሎሽ ሥርዓቱን ማጠናከር ላይ ትኩረት ይሰጣል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ 2030 የእናቶችን በወሊድ ምክንያት የሚከሰት ሞት ከ1 ሺህ መካከል ወደ 70 ዝቅ ለማድረግ እየተሠራ ሲሆን በኢትዮጵያ ደግሞ በጤናው ሴክተር ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሰረት ከ1 ሺህ እናቶች መካከል አሁን ካለበት 401 ወደ 279 ዝቅ ለማድረግ እየተሠራ ነው።

ዜና

# አበዳሪዎች ለታዳጊ አገራት የእዳ እፎይታ የሚያደርጉበትን ጊዜ በግልጽ እንዲያሳውቁ ተጠየቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ አበዳሪዎች ለታዳጊ አገራት የእዳ እፎይታ የሚያደርጉበትን የጊዜ ገደብ በግልጽ እንዲያስቀምጡ ጥያቄ አቀረበች።

የቡድኑ አባል አገራት የብድር ኮሚቴ እ.አ.አ መስከረም 16 ቀን 2021 ባደረገው ስብሰባ የብድር ማገገሚያ(እፎይታ) ስትራቴጂው ላይ ማሻሻያ ማድረጉ የሚታወስ ነው።

ውሳኔው ለኢኮኖሚ ፍላጎቶች ተስማሚ የሆነ ብድር ለማቅረብ እና የታዳጊ አገራትን ማክሮ- ኢኮኖሚ ለማረጋጋት ጠቃሚ እርምጃ መሆኑ በወቅቱ ሲገለጽ ነበር።

የእዳ ተጋላጭነት ለመቀነስ መወሰድ ባለባቸው የፋይናንስ እርምጃዎች ላይ ትኩረቱን ያደረገው ዘጠነኛው የፓሪስ ፎረም ላይ የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር እዮብ ተካልኝ ኢትዮጵያን ወክለው እየተሳተፉ መሆናቸውን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታውቋል።

አበዳሪዎች የቡድን 20 የብድር ማገገሚያ የጋራ ማዕቀፍ መሰረት በማድረግ የእዳ እፎይታውን መቼ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ በግልጽ ማሳወቅና ማዕቀፉን ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው ሚኒስትር ዴኤታው ገልጸዋል።

በፎረሙ ላይ ኢትዮጵያ በጋራ ማዕቀፉ የምታገኘው የብድር እፎይታ(ማገገሚያ) መንግሥት በአጭር ጊዜ ውስጥ የአገሪቷን የእዳ ጫና ለመቀነስ ተግባራዊ እያደረገ ካለው ስትራቴጂ ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ጠይቃለች።

ስትራቴጂው ኢትዮጵያ ያለባትን የብድር ጫና ስጋት ከከፍተኛ ወደ መካከለኛ ዝቅ በማድረግ የተረጋጋ ማክሮ-ኢኮኖሚ ለመፍጠር የሚያስችል ነው ተብሏል።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር እዮብ ተካልኝ ዘላቂ የፋይናንስና የእዳ አስተዳደር ተግባራዊ ለማድረግ መንግሥት አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ቀርጾ ወደ ሥራ ማስገባቱን በመድረኩ ላይ ባደረጉት ንግግር ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜና ሚኒስትር ዴኤታው ዘጠነኛው የፓሪስ ፎረም ስብሰባ ጎን ለጎን ከተለያዩ ባለስልጣናት ባለሀብቶች ጋር መወያየታቸውን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታውቋል።

ዶክተር እዮብ ከፓሪስ ክለብ የጋራ ሊቀመንበር ዊሊያም ሮስ፣ከአሜሪካ ግምጃ ቤት ምክትል ረዳት ጸሐፊና የፓሪስ ክለብ የአሜሪካ ልዑክ ፓትሪሺያ ፖላርድ እንዲሁም ኢትዮጵያ ለዓለም ገበያ ያቀረበችውን የዩሮ ቦንድ ከገዙ ባለሀብቶች በብድርና የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ መምከራቸው ተገልጿል።

የቡድኑ አባል አገራት እና የፓሪስ አበዳሪዎች ክለብ እ.አ.አ 2020 ባሳለፉት ውሳኔ መሰረት እ.አ.አ መስከረም ወር 2021 የኢትዮጵያን የእዳ እፎይታ ጥያቄ የሚመለከት ኮሚቴ መቋቋሙ ይታወሳል።

የአበዳሪ አገራት የጋራ ማዕቀፍ የቡድን 20 አገራትን እና የፓሪስ ክለብ የሚባሉትን አበዳሪዎች በማስተባበር የታዳጊ አገሮችን ዕዳ እንደ የአገሩ ሁኔታ ለማጤን የሚያስችል ስርዓት ይከተላል።



የፓሪስ ክለብ የአሜሪካ፣የእንግሊዝና የፈረንሳይን ጨምሮ የ22 ሀገራትን አበዳሪ ተቋማትን ያካተተ ተቋም ነው።

የብድር ኮሚቴው በቀጣይ በሚኖረው ስብሰባ በኢትዮጵያ ያለው የእዳ ጫና ላይ ትንተና በማቅረብ ምን ያህሉ በእዳ ማገገሚያ ማእቀፍ ውስጥ ይካተት በሚለው ጉዳይ ላይ ምክክር ያደርጋል ተብሎ እንደሚጠበቅ ኢዜአ ዘግቧል።



ሚሪያም አሲ



ተፈሪ ፍቅሬ

## አረንጓዴ አሻራው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አሻራ መርሐግብሮችን በየዓመቱ እያከናወነ ይገኛል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በቀጣይም የችግኝ ተከላና ተያያዥ የስነምህዳር ጥበቃ ሥራዎችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የዲጂታል ኢኮኖሚ አማካሪ ሚሪያም አሊ፤ የአካባቢን ስነምህዳር ለመጠበቅ የሚረዱ የችግኝ ተከላና መንከባከብ ሥራዎች ላይ መሳተፍ ትልቅ ዕድል ነው። ይህን በመገንዘብ ሁሉም ህብረተሰብ የአረንጓዴ አሻራ መርሐግብሮች ላይ በንቃት ሊሳተፍ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

እንደ አማካሪዋ ገለጻ፤ በአገራችን በሚተከሉ ችግኞች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚሰጡና የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመከላከል የሚረዱ ናቸው፤ በዚህ ረገድ እንደአገር የሚታየውን የአካባቢ ጥበቃ ሥራ በተለያዩ ዘርፎች ላይ በጎ ተጽዕኖ ስላለው ሥራውን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል።



ዓለምጸሐይ ጳውሎስ

አቅሙ የፈቀደ ዜጋ ሁሉ የአረንጓዴ አሻራ መርሐግብሮች ላይ እንዲሳተፍና የተከላቸውን ችግኞች እንዲንከባከብም ጥሪ አቅርበዋል።

## "መንግሥት የአገርን ሰላም ለማስጠበቅ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የዜጎችን ሕይወት ለመታደግ ይበልጥ መስራት እንዳለበት የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ ተናገሩ። የመንግሥት ቀዳሚ ተግባር ዜጎችን አስቀድሞ ከጥቃት መከላከል እንጂ ችግር ከደረሰ በኋላ የኀዘን መግለጫ ማውጣት ብቻ መሆን እንደሌለበትም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ ዶክተር ራሔል ባፌ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት ችግር ከተፈጠረ በኋላ የኀዘን መግለጫ ማውጣት ይልቅ መሠራት ያለባቸውን የደህንነት ሥራዎች በመሥራት ዜጎችን አስቀድሞ ከጥቃት መከላከል ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት አለበት።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤትም ሆነ ፓርቲዎች በተናጠል መንግሥት ትኩረት እንዲያደርግ የሚያሳስቡ መግለጫዎችን በተደጋጋሚ ሲያወጡ ነበር ያሉት ዶክተር ራሔል፤ የሕዝብን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ የመንግሥት ተቀዳሚ ሥራ ነው ብለዋል። በመሆኑም መንግሥትም ከሌሎች ፓርቲዎች እኩል ችግር ከተፈጠረ በኋላ መግለጫ ማውጣት ሳይሆን የደህንነት ተቋሙን በማጠናከር ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን ቀድሞ መከላከልና ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ እንደሚጠበቅበት ጠቁመዋል።

በዜጎች ላይ ጥቃት እየደረሰና የአገር ሰላም ስጋት ላይ እየወደቀ ያለው ችግሩ ከመንግሥት አቅም በላይ ሆኖ ሳይሆን መሠራት ያለባቸው የቅድመ ጥንቃቄ ሥራዎች ተሠርተው ወቅታዊ ምላሽ ስላልተሰጠ መሆኑን ያስታወሱት ሰብሳቢዋ፤ መከላከያ ሰራዊትን ጨምሮ የደህንነት ተቋማትና በአጠቃላይም መንግሥት አስፈላጊውን ተግባራዊ እርምጃ በመውሰድ ዜጎችን ከጥቃት መከላከልና የአገርን ሰላም ማስጠበቅ ይኖርበታል ብለዋል።

ፓርቲዎች የሰላማዊ ትግል ታጋዮች እስከሆኑ ድረስ በሰላማዊ መንገድ ሀሳቦችን ወደ ጠረጴዛ የማምጣት ሥራ በመሥራት ለአገር ሰላም መስፈን አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርጉ ጠቅሰው፤ መንግሥት ከሕዝብ የተቀበለውን ኃላፊነት ከተወጣ በኋላ ከሕዝብም ሆነ ከፖለቲካ ፓርቲዎች አስፈላጊውን እገዛ ቢጠይቅ በአገር ጉዳይ ወደ ኋላ የሚል እንደማይኖር ገልጸዋል።

ከሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚጠበቀው ዜጎች ላይ ጉዳት ከደረሰ በኋላ መግለጫ ማውጣት ሳይሆን ቀድሞ ከጥቃት መከላከል ነው ያሉት ዶክተር ራሔል ባፌ፤ ሕዝቡም የራሳቸው ፖለቲካዊ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ወገኖቻቸው ላይ ጥቃት ሲፈጽሙ በአንድነት ቆሞ መከላከልና ለምን ማለት እንጂ ተራ እየጠበቀ በቤቱ መቀመጥ የለበትም ብለዋል። በመሆኑም የአንዱ ቤት ሲነካ ሁሉም በትብብር ሆ ብሎ በመነሳት ወገኑን ከጥቃት መከላከል እንዳለበት ዶክተር ራሔል ባፌ አሳስበዋል።

## እስከአሁን 2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ችግኞች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አረንጓዴ አሻራ፤ በአካባቢ ጥበቃ ውስጥ የሚታዩ ችግሮች እየሰፉ እንዳይሄዱ ያደርጋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በሀገራችን ስኬታማ አካባቢ ጥበቃ በማረጋገጥ ከአፈር ለምነትና አየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ አደጋዎችን በመከላከል ምርትና ምርታማነትን በመጨምር ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ስኬታማ እንደሚያደርግ ገልጸዋል ።

አረንጓዴ አሻራ ጥቅሙ ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸው በዘርፉ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጥራልም ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ የሥራ ባህላችንን እያሻሻልን ጠንክረን ከሰራንበት ሀገራችን ወደፊት በካርቦን ገበያ ገቢ የሚታገኝበት ሁኔታዎችንም ልንፈጥር እንደምንችል አመላክተዋል።

የአረንጓዴ አሻራ ሥራ እውን ከማድረግ ጎን ለጎን በተያዘው ክረምት የፀጥታ ችግር ባሉባቸው ቦታዎች ግብርና ሥራ እንዳይስተጓጎል ከጸጥታ አካላት ጋር በመሆን እየተሰራበት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ አስፈላጊውን የግብርና ግብዓቶች እጥረት እንዳይፈጠርም እየተሰራበት መሆኑን ገልጸዋል። እስከአሁን ድረስ በተሰራው ሥራም የፀጥታ ችግር በሚታይባቸው አካባቢዎች የግብርና ግብዓት በአብዛኛው እንዲደርሳቸው በማድረግ ወደ ማምረት መግባታቸውን ገልጸዋል ።

ምርጥ ዘርና ቴክኖሎጅ አጠቃቀም በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ፍላጎትና ችግሮችን በመለየት የግብርና ምርምርና የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በጋራ የምርምር ሥራዎችን በመስራት ላይ ይገኛሉ ብለዋል።

ከመሰረቱ ግብርናውን ለማዘመንና ወደ ለውጥ መንገድ ሊወስዱ የሚያስችሉ የሥራ ዕቅዶች ከሁለቱም ተቋማት የሚወጡ የምርምር ውጤቶችን መሰረት ያደረገ ነው ብለዋል።

ሁኔታዎች አስቸጋሪ ቢሆኑም በዚህ ሥራ ላይ እየተሳተፉ ያሉ አካላት በሚነፍሰው ንፋስ ሳይደናቀፉ በተለይ ወጣቱ ለኅብረተሰቡ የሚጠቅሙ ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ ጥሪ አቅርበዋል። ሚዲያም ህብረተሰቡን በማነሳሳት ለውጤት የሚያበቁ መልዕክቶችን ለህብረተሰቡ በጊዜው በማድረስ የበኩሉን ሚና እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በተራ አሉባልታና በበሬ ወለደ ትርክት ሕዝባዊ ሰልፉ ሲዛነፍ አይገባም!

ሕዝብ በራሱ ፈቃድ የመረጠውንና ከችግሮቹ አውጥቶ ወደ ተሻለ ነገ ያሻግረኛል ብሎ ያመነበትን መንግስት የመስማትና የመታዘዝ ትልቅ ኃላፊነት አለበት። ይህንን ማድረግ ካልቻለ ከራሱ ተስፋ ጋር ከመጋጨት አልፎ በትውልዶች እጣ ፈንታ ላይ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ከግምት ያለፈ እንደሚሆን ይታመናል።

በተለይም ብዙ ተስፋ ያደረገውን መንግስት በተራ አሉባልታና በበሬ ወለደ ትርክት፤ ክፉዎች በክፋት አምጠው በሚወልዷቸው ከመንገድ በሚያስቀሩ ተስፋ አምካኝ ሀሳቦችና ሀሳቦቹ በሚወልዷቸው ጥፋቶች መሰናከል የለበትም። በገዛ ተስፋው ላይ አፍጥጠው በመጡ ሴራዎች ሊወሰድ አይገባም።

ብዙ ዋጋ ከፍሎ በብዙ ምጥ ከተገላገለው ተስፋውና ከተስፋ መንገድ ተጠልፎ እንዳይወድቅ የተስፋውን መንገዱን በጥንቃቄ መጓዝ፤ በማስተዋልና በስክነት መመላለስ ይጠበቅበታል። እያንዳንዷን ውሳኔ ከተስፋውና ተስፋው ሊያቀናጀው ካለው ተጨባጭ እውነታ ጋር በማስታረቅ ለሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች ከስሜታዊነት እና ግብታዊነት ርቆ መጓዝ ይኖርበታል።

እኛ ኢትዮጵያውያንም ይህንን እውነታ በተጨባጭ ባለመረዳታችን ላለፉት አራት ዓመታት ብዙ ዋጋ ለመክፈል ተገደናል። በብዙ ተራ አሉባልታዎችና በሬ ወለደ ትርክቶች እየተጠለፍን ከፍ ያለ የአቅም ብክነት ውስጥ ለማለፍ ተገደናል። ከተስፋችን ላይ ዓይኖቻችንን በነቀልን ቁጥር ተግዳሮቶቻችንን ሲያንገዳግዱንና እያጋጠሙን ባሉ ፈተናዎች ልክ ተስፋችንን መዘንጋት ሲያጋጥመን ተስተውሏል።

ከለውጡ ዋዜማ ጀምሮ ለለውጥ ኃይሉም ሆነ ለውጡን ለሚመሩት ግለሰቦች/ በግለሰብ ደረጃ የነበረን ድጋፍና በድጋፋችን ውስጥ የነበረው ቁርጠኝነት በአደባባይ ከሞት ጋር እስከ መተናነቅ የደረሰ እንደነበር የሚታወስ ነው። ይህ ቁርጠኛነት በአሉባልታ ነጋዴዎችና በድል አጥቢያ ታጋዮች በብዙ ተፈትኗል። በዚህም ሕዝባችን ውስጥ የተፈጠረው ግራ መጋባትና ግራ መጋባቱ ያስከፈለው ዋጋ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። የተፈጠሩትም መዘናጋቶች ብዙ ናቸው።

ይህ በአሉባልታና በበሬ ወለደ ትርክት የተፈጠረን ሕዝባዊ መዘናጋት በማስፋት ጠላቶቻችን ሕዝቡ ከለውጡ ኃይል ባለፈ በለውጡ መሪዎች/ግለሰቦች/ ላይ ጥርጣሬ እንዲፈጥር ብዙ ሰርተዋል። ይህ መዘናጋት ለባንዳዎችና ለታሪካዊ ጠላቶቻችን ሳይቀር ለጥፋት ተልእኳቸው ዕድል ፈጥሮላቸዋል።

ችግሩ ፓርላማ ድረስ ገብቶ አንዳንድ የፓርላማ አባላቱ ባልተገባ መልኩ ይህንኑ አጀንዳ ሲያስተጋቡ ተስተውለዋል። አደባባይ የሞሉ እውነታዎችን ያልሰማና ያላየ በሚመስል መልኩ ሲንቀሳቀሱም ታይቷል። በዚህም የወከላቸውን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በለውጡ ተስፋ የሚያደርገውን ሕዝብ አሳዝነዋል።

ይህ የጠላትን ሴራ በአግባቡ ካለመረዳት የሚመነጭ የሕዝብ ሰልፍ የማዛባት ንቅናቄ፣ ሕዝብን ከተስፋው ከማራራቅ ባለፈ መንግስትንም ቢሆን እያስከፈለው ያለው ዋጋ ከፍ ያለ ነው። የመንግስትን የትኩረት አቅጣጫ በመከፋፈል ለውጡ በተጀመረበት ፍጥነት እንዳይጓዝ ተግዳሮት ሆኖበታልና።

ከዚያም በላይ የሰልፉ መዛባት ጠላቶቻችን በሕዝባዊ ሰልፍ ውስጥ ሰርገው በመግባት የበለጠ ውጥንቅጥ እንዲፈጥሩና በዚህም ትርጉም አልባ የነበረው ሕልውናቸው ለጥፋት ገንግኖ እንዲወጣ እድል ፈጥሮለታል። ለዚህም በየቀኑ ሕዝባችንን እንደ ሕዝብ እያስከፈለው ያለው ዋጋ ማየት በቂ ነው።

የድል አጥቢያ ታጋዮች እና አገር የማፍረስ ተልዕኮ ያላቸው አንዳንድ ቡድኖች በተለያዩ ስሞች በሕይወቱ ተወራርዶ ለውጡን ባመጣው ኃይል ላይ የሚያካሂዱት የተደራጀ የስም ማጥፋት የሚዲያ ዘመቻ ያሰቡትን ያህል ባያተርፍላቸውም ለታሪካዊ ጠላቶቻችን እና ለባንዳዎች የጥፋት ተልዕኮ የተሻለ እድል መፍጠሩ ግን አልቀረም።

ካለንበት የለውጥ ወቅት አንጻር አንዳንድ ነገሮች መፈጠራቸው ተገማች ቢሆንም፤ የሕዝባችን መንግስትን በአግባቡ አለመስማትና አለመታዘዝ ተስፋውን በሚገዳደርበት ደረጃ ሳይደርስ ሊታረምና የለውጡን ጉዞ ከፍ ወዳለ መንገጫገጭ እንዳይወስድ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል። ችግሩ በራሱ የአደጋ ምንጭ ሆኖ ለውጡን እንዳያጨናግፍም በአግባብ ሊታሰብበት ይገባል።

ሕዝባችን ወዶና ፈቅዶ በአደባባይ በድምጹ ወደ ስልጣን ያመጣውን መንግስት በማዳመጥና በመታዘዝ ለለውጡ ስኬት ያለውን ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አውቆና ተረድቶ ማበርከት ይጠበቅበታል። ለውጡ በልጆቹ የሕይወት መስዋእትነት ፤ በለውጥ ኃይሉ ቁርጠኝነትና መስዋእትነት የመጣና የመጪውን ትውልድ እጣ ፈንታ የሚወስን መሆኑን አስተውሎ በቁርጠኝነት ሊንቀሳቀስ ይገባል።

በተራ አሉባልታና በበሬ ወለደ ትርክት የሚደረግ የሰልፍ መዛባት ከማንም በላይ የሚጎዳው አገርና ሕዝብን ነው። ለታሪካዊ ጠላቶቻችን ዘመን ተሻጋሪ የጥፋት ሴራ ራስን እና አገርን አሳልፎ የመስጠት ያህል ነው። ይህ ደግሞ የቀደመው ዘመንም ሆነ አሁን ያለው ኢትዮጵያዊነት መገለጫ አይደለም!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# ማጭድ እናንሳ!

ዋስልኝ አየለ

**ማጭድ ይሆነን ዘንድ ምንሽር ቀለጠ**
**ዳሩ ብረት እንጂ ልብ አልተለወጠ**
**ለሳር ያልነው ለለት እልፍ አንገት ቀረጠ።**

ሰሞኑን በመገናኛ ብዙኃን የማያቸው ነገሮች ናቸው ይህን የበዕውቀቱ ሥዩም ግጥም ያስታወሱኝ። ባለፈው ሐሙስ ማታ ኢትዮጵያ ቴሌቭዥን አዲስ አበባ ውስጥ ከተለያዩ አካባቢዎች የሕዝብ አስተያየት ያሰባሰበበትን ዜና እያየሁ ነበር። የሁሉም አስተያየት ሰጪዎች መልዕክት የሚያሳየው በጦርነቱ ምን ያህል እንደተማረሩ ነው።

ልብ በሉ! አስተያየቱን የሰጡት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ናቸው። ጦርነቱ በነበረበት አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች ደግሞ ምን እንደሚሉ መገመት በጣም ቀላል ነው። የቤተሰብ አባሎቻቸውን አጥተዋል፣ የእርሻ ማሳቸው የመቃብር ቦታ ሆኗል፣ የስነ ልቦና ጉዳት ደርሶባቸዋል።

እነሆ ያ ጦርነት ሁሉንም የአገሪቱ ክፍል ነክቷል። ይሄ የጦርነት ባህሪ ነው፤ እንኳን በአንዲት አገር ውስጥ ለጎረቤት አገር እንኳን ተፅዕኖ ያደርጋል። ስለዚህ ያ ጦርነት ዳግም እንዳይከሰት የተቻለንን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅብናል።

ባለፈው እሁድ አማራ ቴሌቭዥን ላይ አንድ ድራማ እያየሁ ነበር። ድራማውን የሰራው ሙሉዓለም የአማራ ባህልና ኪነ ጥበባት ማዕከል ከአሚኮ ጋር በመተባበር ሲሆን ደራሲው ሙሐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ነው።

ምንም እንኳን ድራማ የፈጠራ ሥራ መሆኑን ባውቅም፤ እውነተኛ ወካይ መሆኑን የተረዳሁት ገጠርን በሚገባ ማወቄ ነው። ከከብትና ከብት፣ ከውሻና ውሻ፣ ከልጅና ከልጅ.... የሚነሳ ፀብ አካባቢን ሁሉ ያጥለቀልቃል። ይሄ እያየሁት ያደግኩት ነው።

በድራማው ላይ ሁለት ውሾች ይጣላሉ። አንደኛው ልጅ ለውሻቸው አግዞ ሌላኛውን ውሻ ይመታዋል። ውሻው የተመታበት ልጅ ደግሞ ለምን መታህብኝ ብሎ ከልጁ ጋር ይጣላል። ልጆች ሲጣሉ እናቶች ይመጣሉ። እናቶች ሲመጡ ባሎቻቸው ይጣላሉ። ባሎቻቸው ሲጣሉ የባሎቻቸው ጓደኞች ለየጓደኞቻቸው ያግዛሉ። እንዲህ እንዲህ እያለ ወደ አካባቢና ጎሳ ያድጋል። ከዚያም ወደ ብሔር።

ከዚህ የምንረዳው ነገርየውን ከውሾችና ከልጆች ፀብ ላይ እያለ ማስቀረት ይቻል የነበረ መሆኑን ነው።ውሾች ምንም አያውቁም፤ አጥንት ያጣላቸዋል። ልጆችም እንደዚያው፤ ልጆች ናቸውና አያውቁም፤ አዋቂዎች ግን እዚያው ላይ ማስቆም ነበረባቸው።

የዕውቀቱ ሥዩምን ግጥም መነሻ በማድረግ ወደ ዋናው ጉዳይ እንግባ። ምንሽርን ወደ ማጭድ መቀየር የሚቻለው አስተሳሰብ ሲቀየር ነው። ከጦርነት ምኞትና ሀሳብ እንውጣ።‹‹ጦርነት ማን ይመኛል?›› ይባል ይሆናል። ዳሩ ግን ጦርነትን የሚመኙ አይተናል። ከዳር ሆነው ‹‹ግፋ በለው!›› የሚሉ ብዙ ናቸው።

ከሰሜኑ ጦርነት በፊት ስለ ሰላም ብዙ ተብሏል።ለሰላም ቅድሚያ ለመስጠት ያልተደረገ ነገር የለም።ምንሽር ይቅርና ማጭድ እንያዝ ተብሎ ነበር። ዳሩ ግን አስተሳሰብ አልተቀየረምና ምንሽሩ ወደ ማጭድ ስላልተለወጠ የብዙዎችን አንገት ቆረጠ።

ምንሽርን ወደ ማጭድ ለመቀየር በግለሰብ ደረጃ እንኳን ብዙ ተለፍቷል። በቀልድም በቁም ነገርም ‹‹እንደዋዛ ገንዘብ አያባክንም›› እየተባለ የሚነገርለት አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ በግሉ አውሮፕላን ተከራይቶ ሽማግሌዎች ይዞ መቀሌ ሄዷል። በሕይወቱ አውሮፕላን የተከራየው ለዚያ ጉዳይ ብቻ እንደሆነ በአንድ ቃለ መጠይቅ ላይ ሲናገር ሰምቻለሁ። ከአገር በላይ ምንም ስለሌለ በወቅቱ የትኛውንም ነገር አደርግ ነበር ብሏል።

ያ ሁሉ ሳይሳካ ቀርቶ ምንሽሩ ወደ ማጭድ ሳይቀየር ቀረ።እነዚያ ያየናቸውና የሰማናቸው ግድያዎችና ውድመቶች ደረሱ። መፈናቀል በዛ፤ ለኑሮ ውድነቱም አሉታዊ ጫናውን አሳረፈ።

አሁን ያለፈው አልፏል። ከዚያም ከዚህም ያለው ወገን ‹‹ግፋ በለው!›› ማለት ይብቃው። ሁሉም ጥፋትን አይቶታል። በተለይም የአገር ውስጥ ጦርነት ሲሆን ደግሞ አደጋው የከፋ ነው። በተለይም በክረምት የግብርና ሥራ ላይ የተመሰረተውን የአገሪቱን ኢኮኖሚ የከፋ ቀውስ ውስጥ ይከተዋል፤ ይሄ ደግሞ ጦሱ ለሁሉም ነው። ስለዚህ የጦርነት ዳፋ ለሁሉም ይተርፋል፤ እነሆ ተርፎም አይተነዋል።

ስለዚህ ይጀመራል ለተባለው ድርድር ሁላችንም አዎንታዊ አስተዋፅኦ ልናበረክት ይገባል። የሃይማኖት አባቶች፣ የተለያየ ዘርፍ ባለሙያዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን አለባቸው።

ለሰላም አወንታዊ አስተዋፅኦ ስናበረክት ብዙ ነገሮችን ችለን መሆን አለበት። ከጦርነቱ አትራፊዎች በሚሰድቡን ስድብ ሁሉ መደንበርና መዋዥቅ የለብንም። እነርሱ የሚፈልጉት ሌላ ፖለቲካዊ ትርፍ ስላላቸው ነው።

ሰው ሆኖ ሰላምን የማይፈልግ የለም፤ ዳሩ ግን ቡድናዊ ጥቅም ብቻ የሚያስቡ ኃይሎች ደግሞ አሉ።በእነዚህ ኃይሎች ድርድሩ አይደገፍም።ሌላም ሰው እንዳይደግፈው የተለያዩ አሸማቃቂ ነገሮችን ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፤ ‹‹በዚህ ጊዜ እንዲህ ብላችሁ ነበር፣ ያኔ እንዲህ ስትሉ ነበር....” የሚሉ ሙግቶችን ያመጣሉ። ይሄኔ የድርድሩ ደጋፊዎችን ሊያሳስብ የሚገባ መሆን የለበትም። ምክንያቱም እነዚያ ቡድናዊ ጥቅም አስጠባቂዎች የራሳቸውን ሥራ እየሰሩ ነው።

ሁላችንም ለሰላም ቅድሚያ ሰጥተን ዳግም ጦርነት እንዳይኖር ካላደረግን፤ ለልጅ ልጆቻችን አሳፋሪ ታሪክ ነው የምናስተላልፈው። ይህን እያንዳንዱ ዜጋ ልብ ሊለው ይገባል። ዕድለኛ ሆኖ በአዛውንትነቱ ከልጅ ልጆቹ ጋር ስለወጣትነቱ የሚያወራበት ዕድል ቢያገኝ የሚያኮራ ታሪክ ነው ማውራት ያለበት። በዚህ የቴክኖሎጂ ዘመን እያንዳንዱ መረጃ ተሰንዶ ነው የሚቀመጥ። ስለዚህ በአዛውንትነት ዕድሜያችን ‹‹እናንተ ናችሁ እንዲህ ያደረጋችሁ አይደል?›› መባል የለብንም።

ያለፈው አልፏል። ከዚያ በኋላ ያለውን አሳምረን፣ ያለፈው ልክ እንደ አንድ የታሪክ አጋጣሚ ብቻ ‹‹እንዲህ ተደርጎ ነበር፤ ዳሩ ግን በድርድር ሰላም ሆነ›› መባል አለበት። ድርድር፣ ሰላምና እርቅ፣ ይቅር ባይነት... የኢትዮጵያ አኩሪ እሴቶች መሆናቸውን አስቀጥለን ማሳየት አለብን።

በአዛውንትነት ዕድሜያችን በአገሪቱ ውስጥ የሆነ ነገር እንኳን ቢከሰት፤ እንደ ምሳሌ የምናነሳው ጥሩ ተሞክሮ ማኖር አለብን። ልክ ዛሬ ‹‹አባቶቻችን እንዲህ አድርገው ነው ያቆዩልን›› እንደምንለው ሁሉ፤ እኛም ‹‹እንዲህ አድርገው፣ ይህን ሰርተው ነው ያቆዩዋት›› መባል አለብን። የአባቶቻችን ፈለግ መከተል ብቻ ሳይሆን እኛም ተከታይ ማፍራት አለብን።

መንግሥትም በቆራጥ ውሳኔ ድርድሩን መቋጨትና ሰላምን ማምጣት አለበት። አለበለዚያ በአስተዳደር ዘመኑ መጥፎ ታሪክ ይመዘገባል። እስከ አሁን የሆነውን ‹‹በለውጥ ወቅት የሚያጋጥም ነው›› ቢባልም ከዚህ በኋላ የሚሆነውን ግን በለውጥ ወቅት የሚያጋጥም ነው ብሎ ለመቀበል አያስችልም።

መገናኛ ብዙኃን የጦርነት አዋጅ ነጋሪነት ሊበቃቸው ይገባል። አገሪቱ ከውጭ በኩል ብዙ ስጋት የተጋረጠባት ናት። ስለዚህ የአገር ውስጥ አንድነት መኖር አለበት። ስለዚህ ደግሞ ሁላችንም መበሻሸቅንና መጠላለፍን መተው አለብን። እውነተኛ የአገር ስሜት ያለው ከወገኑ ጋር አይጣላም። ስለዚህ ከድርድር፣ ለእርቅና ይቅር ባይነት ሁላችንም ቅን እንሁን። የኑሮ ውድነት የሚያደርገውን እያየን ነውና ማጭድ እናንሳ!

## ነፃ ሃሳብ

# መስጠት ከመስጠት በላይ ነው!

**በአክበረት ታደሰ**

መስጠትና መቀበል በሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ አካላት መካከል የሚደረግ ግንኙነት ነው። ይህም ያለው ለሌለው በመስጠት። የሌለው ካለው በመቀበል እንዲሁም እርስ በእርስ የመመጋገብ ሂደት ነው።በመሆኑም ሁላችንም በዚህ የህይወት መንገድ ውስጥ እናልፋለን።እንሰጣለን እንቀበላለን።አስበነውም ይሁን ሳናስበው በዚህ ሂደት ውስጥ ማለፋችን የግድ ነው።

በኢትዮጵያውያን የክርስትና እምነት ተከታዮች መፅሀፍ ቅዱስ። በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ቁርኣን አብዛኞቻችን የህይወት መንገድና መመሪያ አድርገን የምንጠቀምባቸው መጻሐፍት ናቸው። የሁሉም ቤተ እምነቶች መመሪያ በሆነው ታላቁ መፅሀፍ፤ መስጠት የህይወት አንድ አካል መሆን እንዳለበት። በመስጠት ውስጥ ትልቅ መንፈሳዊ በረከት እንደሚገኝ ይመክራል። በመጽሀፍ ቅዱስ ተመዝግቦ የምናገኘው የሀዋርያት ስራ 20፡-35 "ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብጹእ ነው"። ይላል ። በዚህ ቃል ላይ የሚሰጥ አለ የሚቀበል አለ። በዚህ ግንኙነት ውስጥ ሰጪው ከተቀባዩ ይልቅ ዋጋው ትልቅ እንደሆነ ያስረዳናል።

ይህም የሚያሳየው ማንም ሰው ሊቀበል ይችላል።ለመቀበል የተለየ ልብ አይጠይቅም።ለመቀበል ምንም አይነት ጉልበት አያስፈልግም።ለመስጠት ግን የተሰጠ ልብ ይጠይቃል።የሚሰጥ ልብ የታደለ ነው።ምናልባት የሚሰጠው ነገር ስለተረፈው ላይሆን ይችላል።ከጉድለቱም ይሆናል የሚሰጠው ዋናው ነገር ለመስጠት የተነሳበት ልብ ነው።ዋጋ ያለው መስጠት ደግሞ ስንሰጥ የማንፈልገውንና የተረፈንን ሳይሆን የሚያስፈልገንን በማካፈል ነው ።ምክንያቱ ደግሞ በሉቃስ መጽሀፍ 21፡-2፡-4 " አንዲት ድሀ መበለት ሁለት ሳንቲም በዚያ ስትጥል ጌታ ኢየሱስ አየና እውነት እላችኋለው ይህች ደሀ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች እነዚህ ሁሉ ከትርፋቸው ወደ እግዚአብሄር መዝገብ ጥለዋልና ይህች ግን ከጉድለትዋ የነበራትን ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አለ"።ሴቲቱ ድሀ መበለት ብትሆንም ያላትን ሁሉ ነበር የሰጠችው።

ስንሰጥ የስጦታው መጠን ሳይሆን የሚታየው የሰጠንበት ልብ ነው። ደግሞም በምንሰጥበት ወቅት ደስ እያለን።ልባችን ሀሴት እያደረገ መሆን አለበት እንጂ እያዘንን። ቅር እያለን። ጉድለት እየተሰማን መሆን የለበትም።ከእንደዚህ አይነት መስጠት አለመስጠት ይሻላልና። በታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ የሮሜ መጽሀፍ 12፡-8 ላይ "የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ።የሚሰጥ በልግስና ይስጥ። የሚገዛ በትጋት ይግዛ የሚምር ቢኖር በደስታ ይማር"።ይላል በመሆኑም ስንሰጥ ደስ እያለን በልግስና መሆን ይገባዋል።

ደግሞም ሰጥቶ የሚጎድልበት የለም በእጥፍ ይቀበላል እንጂ።ሰጥተን አናጣም።ያለንን ስናካፍል የመስጠት ልባችንን የሚያይ ፈጣሪ ደግሞ አብዝቶ ይሰጠናል።ፈጣሪ በብዙ ነገሮች ሲባርከን በሀብት፤ በእውቀት፤ በጉልበት። በጥበብ ለራሳችን ብቻ እንድንጠቀምበት አይደለም። ሌሎችንም እንድንጠቅምበት እንጂ። ሁላችንም እንደምናምነው ፈጣሪ አንደኛችንን በምቾት እያንደላቀቀ። የምናስቀምጥበት እስክናጣ ድረስ ተትረፍርፈን እየኖርን። ሌላኛው ወንድማችን ደግሞ አንድ ጉርሻ ናፍቆት እንዲኖር የሚፈርድ ኢፍትሃዊ አምላክ አይደለም።ማወቅ ያለብን ሲሰጠን እንድናካፍል ያለንን ለሌላው እንድንሰጥ ነው።ነፍሱን እስከመስጠት የወደደን ፈጣሪ ባለንጀሮቻችንን እንድንወድ ትእዛዝ የሰጠንም ለዚሁ ቅዱስ ዓላማ እንደሆነ ጥርጥር የለውም።

አምላክ ሰው ሆኖ መጥቶ እኛን ለማዳን ነፍሱን በመስጠት ህይወትን ሲሰጠን። በዛውም የመስጠትን ጥግ እያሣየን ነው።መስጠት ምን ድረስ እንደሆነ እያስተማረን ነው። ስንወድ ምትክ የሌለውን ነገር እስከመስጠት እንደሚሆን አሳይቶናል። መስጠት ብዙ አይነት ።ሁሉም ሰው የመስጠት ልብ ይኑረው እንጂ የሚሰጠው ነገር አያጣም።በመቀጠልም ጥቂት የመስጠት (የስጦታ) አይነቶችን እንመልከት።

### ፍቅርን መስጠት

ፍቅር ከልብ የጠለቀ የመውደድ ኃይል ነው።ፍቅር የምግባራት ሁሉ አለቃ ነው።የነገሮች ሁሉ ራስ ነው።ፍቅር ታላቅ የመንፈስ ፍሬ ነው።የሚጀምረው ደግሞ ከቤተሰብ ነው።አንድ ሰው ወደዚህች ምድር ሲመጣ በመጀመሪያ የሚተዋወቀው ከወላጆቹ (ከቤተሰቦቹ) ጋር ነው።በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ የመጀመሪያው ፍቅር የቤተሰብ ፍቅር ነው። ከቤተሰቡ በመቀጠል አንድ ሰው እድሜው እየጨመረ።ማህበራዊ ግንኙነቱ እየሰፋ ሲመጣ የሚወዳቸው የሚኖርላቸው ሰዎች (ነገሮች) ቁጥር እየጨመረ ይመጣል።

በዘመናችን ደግሞ ይህ የመንፈስ ፍሬ የሆነው ፍቅር ቀዝቅዟል። ከሰው ልጅ ልብ ላይ የተሰረዘም ይመስላል።ምክንያቱም በተጨባጭ እያየን ያለነው ይህን በመሆኑ ነው።ሰው ተጨካክኗል፤ ራስ ወዳድነት ነግሷል። መከፋፈል።መለያየት አየሩን ተቆጣጥሮታል።አለምን ትተን አሁን አገራችን ላይ እየሆነ ያለውን ብንመለከት የችግሩ ሁሉ ምንጭ የፍቅር መቀዝቀዝ ውጤት መሆኑን እንረዳለን።

እርስ በእርስ መገዳደልን ጨምሮ ብዙ ዘግናኝ እና ሰቅጣጭ እግዚአብሄር በአምሳሉ ለፈጠረው ለሰው ልጅ የማይገባ አሟሟትና አገዳደል እያየን ነው።ታዲያ ከዚህ በላይ ፍቅር መቀዝቀዙን የሚያረጋግጥ ምን ነገር ሊመጣ ይችላል።ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስን በደብረዘይት ተራራ ስለአለም ፍጻሜ ሲጠይቁት ምልክቱን ሲነግራቸው በሰው ልጅ ዘንድ ፍቅር እንደሚቀዘቅዝ አሳስቦ ነበር። 1ኛ ጴጥሮስ 4፡-8 ላይም "ትጸልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ ፍቅር የሀጥያትን ብዛትን ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በእርሳቹ ተዋደዱ"።ይላል ይህም ከሚመጣብን ክፉ ነገር ማምለጫ መንገዳችን ፍቅር ብቻ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው።ይገርማል ፍቅር በፈጣሪ ፊት የበደልነውን በደላችንን የማስተሰረይ የመሸፈን አቅም አለው።ያለዋጋ ያለድካም ልናደርገው የሚገባን ድንቅ ስጦታ ፍቅር ነው።

ለወጥ ማጣፈጫ ጨው እንደሆነ ሁሉ።በብዙ ጥንቃቄ በብዙ ቅመማቅመም የተሰራ ወጥ ጨው ካልተጨመረበት ጣእሙ እንደማይታወቅ። የሰው ልጅ ህይወትም ብዙ ነገሮች ቢኖሩትም። በቁሳዊ ነገር ተሳክቶልኛል ብሎ ቢያስብም በህይወቱ ፍቅር ከጎደለው ግን የነዚህን ነገሮች ሁሉ ጣእም ማወቅ አይችልም።ሁሉ ኖሮን ፍቅር ግን ከሌለን ከንቱ ነን እንዲል ታላቁ መጽሐፍ።

የህይወት ማጣፈጫ ቅመም ፍቅር ነው።እግዚአብሄር ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር በልጁ በኩል ገልጧል።እርሱም ቅድመ ዓለም የነበረ የባህርይ ውድ ልጁ እየሱስ ክርስቶስ ነው።እየሱስ ፍፁም ፍቅሩን ካሳየን በኋላ በዮሀንስ 15፡-12 ላይ "እኔ እንደወደድኋችሁ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት"። ሲል እርሱ እንደወደደን እኛም እንዋደድ ዘንድ አዞናል።ሰው እለት እለት በፍቅር የጋለና የተነቃቃ መሆን አለበት። ሰውን መውደድ ማለት ስለዛ ሰው መልካም ማሰብ።መልካም መመኘት እንዲሁም ለዛ ሰው መንገድ መቃናት።ህይወት መሳካት የምንችለውን ሁሉ ማድረግ ማለት ነው።

ይህ ደግሞ ቅንነት የተሞላ ሀሳብ ነው። ውስጣችን በዚህ ሀሳብ ሲሞላ የሚሰማን ሰላም እና እረፍት ነው።ለሰዎች መልካም በማሰብ ውስጥ የሚገኘው እርካታ ከምንም ጋር አይወዳደርም።አሁን በተጨባጭ ያለው ግን የሚያሳዝን ነው።ሰዎች የራሳቸውን ህይወት እንዴት ስኬታማ ማድረግ እንደሚችሉ ሳይሆን የስኬታማ ወዳጃቸውን ስኬት እንዴት እንደሚያጠፉ በማሰብ አእምሯቸው ተይዟል።ይህ የፍቅር ማጣት ምልክት ነው።የጥላቻ ስሜት እንኳን ለሌላው ለራስም ምቾት አይሰጥም። የሰው ልጅ በሕይወቱ ደስተኛ መሆን ከፈለገ ከጥላቻ መራቅ አለበት። ሰላማዊ ኑሮ ለመምራት በእምነት ድር እና በፍቅር ማግ የተገመደ ህይወት ሊኖረን ይገባል።

በታላቁ መጽሐፍ "እንዲህም ከሆነ እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሶስቱ ፀንተው ይኖራሉ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው" ይላል። ፍቅር የምንተርከው ሳይሆን የምንኖረው ህይወት ነው።የነገሮች መቋጫ ማሰሪያ እውነተኛ ፍቅር ነው። ፍቅር ለሰዎች መልካም መሆን የሚጠሉንን እንኳን ቢሆን መውደድ ነው።" ጠላቶቻችሁን ውደዱ ለሚጠሏችሁ መልካም አድርጉ" የተባለውም ለዚሁ ነው። የወደዱንን ብንወድማ ምንም ቸርነት አላደረግንም። የወደደውን የማይወድ ማን አለ? ነገር ግን የሚጠሉንንም በመውደድ የሚረግሙንን በመመረቅ በፍቅር መግዛት።ማሸነፍ ነው ትልቁ ቁምነገር።

### ምፅዋት መስጠት

የምፅዋት ስርወ ቃል የመጣው ከግእዝ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም ስጦታ።ልግስ።ችሮታ ማለት ነው።አንድ ሰው በሌላኛው ሰው ላይ የሚያየውን ማጣት፣ችግር በማስተዋል በፍፁም ርህራሄና ፈቃ፣የተቸገረበትን ነገር መርዳት፣ ማገዝ፣ መስጠት፤ በጎ ስጦታ ወይም ምፅዋት ይባላል።ፈጣሪ ከሰጪዎች ጋር የሚሰጥ ከተቀባዮች ጋርም የሚቀበል ነው።በመስጠትና በመቀበል በሰዎች መካከል መተሳሰብና መረዳዳት እንዲኖር።ሀብትን ለሀብታሞች ሲሰጥ ከእነርሱ የሚያንሱትን እንዲያግዙበት( እንዲያስተናግዱበት) ነው።ምፅዋት የእለት ምግብና የአመት ልብስ ለቸገራቸው ሰዎች ገንዘብ መስጠት፣ ደግሞም ምክር ለቸገራቸው መምከር፣ትምህርት ለቸገራቸው ማስተማር ነው።ምንጭ፡- ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደስላሴ ጎሐ ፅባህ መፅሀፍ።

ጠቢቡ ሰለሞን በመፅሀፈ ምሳሌ 19፡-17 "ለድሀ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሄር ያበድራል በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል"። ይላል ይህ ጥቅስ ምፅዋት ብልሆች በእግዚአብሄር ዘንድ የሚያስቀምጡት አደራ መሆኑን ይነግረናል። በዚህች ዓለም ስንኖር ማጣትም ማግኘትም በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ይፈራረቃሉ። ያልተማሩትን በእውቀት።የሙያ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን በሙያ። ደካሞችን በጉልበት ማገዝ ተገቢ እና ቅዱስ ተግባር ነው።

ደግሞም ስንሰጥ ከተረፈን ነገር ሳይሆን ካለን።ከሚያስፈልገን መሆን ይገባዋል።መስጠት ሰው የመሆን ትልቅ ቁልፍ ነውና። አብዛኞቻችን የሀጥያት መሰረት በተባለው በነዋይ ፍቅር። በገንዘብ መውደድ ልባችን ስለታሰረ።መስጠት የሚመስለን ከተትረፈረፈው ኪሳችን አንድ ብር ለነዳይ መመጽወት ነው።ነገር ግን መስጠት ከጉድለታችን ነው።በሌላ አነጋገር በዝቶ የተትረፈረፈ ብዙ ዓይነት ምግብ በልተን የተረፈንን መስጠት ሳይሆን፤ አይነቱን ቀንሰን የሌለው ወንድማችንም እኛ የምንበላውን እንዲበላ ማድረግ ነው።

የተቀደደ እና የማይጠቅመውን ከመስጠት ይልቅ ካልተበላሹ ልብሶቻችን ውስጥ ለተቸገሩት መስጠት ነው ተገቢው ነገር። ምክንያቱም ያም ነዳይ ቀን ጥሎት ተቸግሮ እንጂ በእግዚአብሄር አምሳል የተፈጠረ። እኛ የሚገባን የሚገባው ክቡር የሰው ልጅ ነውና። ስንሰጥ በንፁህ ልብ፤ በልግስና፤ ባለመመፃደቅ ከከንቱ ውዳሴ፤ ከታይታ በፀዳ መልኩ መሆን ይገባዋል። ከዚህም ባለፈ ምላሽ መጠበቅም የለብንም።

ምፅዋት የሚሰጡ ሰዎች የሚጠቀሙትን ያህል የማይሰጡት ደግሞ ይጎዳሉ።የመጀመሪያው መስጠት የፈጣሪ ህግ በመሆኑ እሱን ባለመፈፀም ይጠየቃሉ።ሌላው ደግሞ ከመስጠት የሚገኘውን እርካታ ለማወቅ አልታደሉም። በመስጠት ውስጥ የሚገኝ ትልቅ ደስታ አለ። የተሰጠውን ሰው ደስታ ማየት በራሱ የሚሰጠው እርካታ ልዩ ነው።ለሰው መስጠት ማዘን። መራራት። ከፈጣሪ የሚሰጥ ትልቅ መንፈሳዊ በረከት ነው።በሉቃስ መጽሀፍ 6፡- 38 "ስጡ ይሰጣቹሁማል በምትሰፍሩት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላቹሀል" ይላል።የሚሰጥ ይሰጠዋል።

አንድ አባት ስለመስጠት ሲያጫውቱኝ። አንዳንድ ጊዜ ከቤታችን ያለው ነገር ሞልቶ። የሰው ልጅ ፍላጎት አያልቅምና ፈጣሪ እንዲጨምርልን የተሻለ ነገር እንዲሰጠን እንደክማለን እንለምናለን።ግን ደግሞ የልብስ ማስቀመጫችን በቆዩ ልብሶች ተጨናንቋል። ቤታችን ውስጥ የሚያስፈልጉን እቃዎች በሙሉ አሉ ግን የተሻለ ነገር እንፈልጋለን።ሌላ ብናገኝ የምናስቀምጥበት ቦታ እንኳን የለንም።

ፈጣሪ የምንሰራውን ነገር እንዲባርክልንና በተሻለ ነገር እንዲቀይርልን ቤታችን ውስጥ ያሉትን ቆዩ፣ ሰለቹን ያልናቸውን እቃዎች አውጥተን ለሌላቸው፣ እኛ ሰለቸን ያልነው ለሚናፍቃቸው መስጠት ይገባናል።ያን ጊዜ እግዜሩም ሲሰጠን የምናስቀምጥበት እናገኛለን። መጀመሪያ ለመቀበል የሚሆን ቦታ እናስለቅቅ ብለው አስገርመውኛል።እውነት ነው አብዛኞቻችን በዝቶብን የማንጠቀምባቸው ትርፍ እቃዎች አሉን። አዲስ የተሻለ ነገር እንዲጨመርልን ቦታ ማስለቀቅ አለብን።አንዳንዶቻችን ደግሞ ለማን መስጠት እንዳለብን ማወቅ አለብን። ስጦታችን ዋጋ የሚኖርበት ቦታ ላይ ብናውለው መልካም ነው።

በጎ ላልሆነ ዓላማ ለሚያውል፡ ለቁማር፤ አደንዛዥ እፅ ለመጠቀም ወይም ያለአግባብ ከልክ በላይ ለሚጠጣ ሰው ገንዘባችንን ብንሰጥ መስጠታችን ተገቢ አይሆንም። ስለሆነም ስንሰጥ ለማን እንስጥ የሚለው ልዩ ትኩረት ይፈልጋል ማለት ነው። በሌላም በኩል የውጭ አልጋ የቤት ቀጋ እንደሚለው ብሂል የራሳችንን ቤተሰብ እየበደልንና ለቤታችን ማድረግ የሚገባንን ሳናደርግ የቤተሰባችንን ፍላጎት ችላ ብለን ለሌላው መስጠትም አስፈላጊ አይደለም።

### ስምንጠየቀው ጥያቄ ተገቢ የሆነ ምላሽ መስጠት

በተለያዩ አጋጣሚዎች ከተለያዩ አይነት ሰዎች የተለያዩ ጥያቄዎች ልንጠየቅ እንችላለን። በዚህ ጊዜ ተገቢውን መልስ በተገቢው መልኩ በማክበር። በትህትና መልስ መስጠት አለብን።የተጠየቅነውን ነገር በማወቃችን ልንታበይና ልንኩራራ አይገባም።ሁሉም ሰው በየዘርፉ የተለያየ እውቀት ሊኖረው ይችላል። ሁሉም ሰው ግን ሁሉም ነገር ላይ እኩል እውቀት ሊኖረው አይችልም።በመሆኑም እኛም የማናውቀው።እርዳታ የምንፈልግበት ጉዳይ ሊኖር ይችላልና ሰዎች ያልቻሉትን። ያላወቁትን ነገር ሲጠይቁን በትህትና ማሳየት መንገር ነው የሚገባን።እነዚህን ነገሮች መፈፀም የአንድ መልካም ሰው መገለጫ በተለይ ከአንድ ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ ነገር ነው።

በተሰጠን ጸጋ በተሰጠን እውቀት ባገኘነው ነገር ሁሉ ያለስስት ማካፈል ያለመታበይ መስጠት ያስፈልጋል ይህንን ማድረግ ዋጋው ታላቅ ነው።በመጨረሻም በፈቃደኝነትና በትክክለኛ የልብ ዝንባሌ ተነስተን እንስጥ።እንዲህ ባለ ዝንባሌ ተነሳስቶ መስጠት ተቀባዩን ብቻ ሳይሆን ሰጪውንም ይጠቅማልና።

ከላይ ልዩ ልዩ ጥቅሶችንና የአባቶችን ምክር አክዬ ለማስረዳት እንደሞከርኩት መስጠት በምድርም ሆነ በሰማይ ዋጋ ያለው ትልቅ ተግባር መሆኑን ተመልክተናል። ሰሚና አንባቢ ብቻ ሳይሆን አድራጊም ሁኑ እንዲል ቅዱስ መጽሓፍ ሁላችንም እንደየአቅማችን በንጹህ ልብ ቤተሰብ ጎረቤትና ዜጋን በመስጠት መጎብኘት ይጠበቅብናል። በተለይ በተለይ ደግሞ ሁሉ ነገር ጨለማ በሚመስለብት በዚህ ክረምት እየተተገበረ ባለው የአቅመ ደካሞችን ቤት መገንባትና ማጋራት ላይ መሳተፍ ሊያመልጠን የሚገባ ዕድል መሆን የለበትም እላለሁ። ሰላም ።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን በወፍ በረር

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ በሳይንስና ቴክኖሎጂው እንዲሁም በዲጂታል ኢኮኖሚው ተጨባጭ ለውጥ ለማስመዝገብ በማለም መንገድ ጠራጊ በሆኑት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ልዩ ልዩ መመሪያዎች ላይ በትኩረት እየሰራች መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። በተለይ በዘርፉ ልዩ ክህሎት ያላቸው ወጣቶችንና ታዳጊዎችን ለማብቃት የሚያስችሉ የልህቀት ማእከላትም ወደ ስራ ለማስገባት የሚሰሩ በርካታ መሬት ላይ የወረዱ ስራዎችን ይታያሉ። ይህንን የተግባር ስራ በሚፈለገው ፍጥነትና የጥራት ደረጃ ለመስራት ደግሞ መንግስት የተለያዩ ስትራቴጂዎች በመንደፍ ስራ ላይ አውሏል። ከእነዚህ ውስጥ “ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ» አንዱ ነው። በዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ አምዳችን ስትራቴጂው በዝርዝር ምን ይዘቶች እንዳሉት በወፍ በረር እንቃኛለን።

ይህ ስትራቴጂ በዋናነት “የቴክኖሎጂ ለውጥ ለማህበራዊ እድገት፣ ምርታማነት ለማሻሻል እና ሁሉን አቀፍ እድገት ለማምጣት ወሳኝ ሚና እንዳለው እሙን ነው” የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ ነው። በተለይ ዓለማችን የቀጣዩን የቴክኖሎጂ ለውጥ እውን ለማድረግ በዋዜማው ላይ ትገኛለች ይላል። ቴክኖሎጂው በእድገት ደረጃ ላሉ አገራት የተለያየ ዓይነት ምቹ አጋጣሚንም እንደሚፈጥርላቸው ያብራራል።

“ዋናው ጉዳይ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚመረጠው መንገድ በዋናነት ከአገራዊ ርዕይ እና ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ብሔራዊ የልማት አጀንዳዎች ጋር የጠበቀ ቁርኝት ሊኖረው ይገባል” የሚለው ሀሳብ በስትራቴጂው ሰፍሯል፤ በዚሁ መሰረት የኢትዮጵያ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ በአገር ውስጥ ከአገር በቀል የምጣኔ ሀብት ተሃድሶ አጀንዳ እና እየተተገበረ ከሚገኘው ከአስር ዓመቱ የልማት እቅድ (2013 እስከ 2022 ዓ.ም) ጋር፤ ከዓለም አቀፍ አንጻር ደግሞ ከተባበሩት መንግስታት የዘላቂ ልማት ግቦች እና ከአፍሪካ ህብረት አህጉራዊ የዲጂታል ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ መሆን እንዳለበት አፅእኖት ሰጥቶ ይገልጻል።

እነዚህ መሪ የመንግስት ሰነዶች የማክሮ-ኢኮኖሚ መዛባትን ለማስተካከል፣ የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ችግር ለመፍታት፣ የተመጣጠነ ሁሉን አቀፍ ብልጽግና ለማምጣት፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ዘርፎች ለመለየት እና በሂደትም ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆንበት፣ በእውቀት ላይ የተመሰረተ እና የበለጸገ ህብረተሰብ ለመፍጠር ያለሙ መሆናቸውንም ነው የሚያብራራው።

ኢትዮጵያ በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ አዲስ አብዮት ለመፍጠርና እድገቷን በዚያ ላይ ለመገንባት ቆርጣ ወደ ትግበራ ገብታለች። ሁሉም ቁልፍ ዘርፎች ዘመኑ የሚጠይቀውን ሳይንሳዊና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንዲከተሉም የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛል። በእርግጥ ዓለም በዘርፉ ከደረሰበት የላቀ ደረጃ አንፃር ያለውን የአገሪቱን አፈጻጸም ስንገመግም ወደኋላ ከቀሩት የዓለም አገሮች ጋር የምትመደብ መሆኗ እሙን ነው። ይሁን እንጂ ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ ተስፋ ሰጪ ጥረቶችን እየተመለከትን ነው። ለእዚህም በግብርናው ዘርፍ ላይ በጎ ውጤት ሊያስከትል የሚችለውን የሳተላይት ቴክኖሎጂን፣ የቴሌኮም አገልግሎቶችን፣ የክፍያ ስርአቶችን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል።

መንግስት “ለሳይንስና ቴክኖሎጂ” ዘርፍ ልዩ ትኩረት መስጠቱን በርካታ ማረጋገጫዎችን ማግኘት ይቻላል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳይንስና ቴክኖሎጂን አስመልክተው እንዳሉት፤ ዓለም ባልተጠበቀ ፍጥነት አራተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት እያካሄደች ትገኛለች። ሕዝቡ ከዚህ ክስተት ተጠቃሚ እንዲሆን በተለይ ወጣቶች በአዲሱ የዓለም ሥርዓት ውስጥ ስኬታማ እንዲሆኑ ኢትዮጵያ በትኩረት መሥራት ይጠበቅባታል። በአሁኑ ወቅት እንደ ሰው ሰራሽ አስተውሎት (Arteficial Intelegence)፣ የበይነ መረብ ቁሶች (Internet of things)፣ ናኖ ቴክኖሎጂ፣ እና ውሒብ አስተኔ (Big Data) ባሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የሚደገፉ የማምረት፣ የመገናኛ እና የአኗኗር ዘይቤ ሽግግሮችን እየተመለከትን ነው። ታዳጊዎች አዳዲስ ክህሎት እና ዕውቀትን ይፈልጋሉ፤ የወደፊቱን ጊዜ በተሻለ




ለመጠቀም እንዲችሉ ማድረግ ደግሞ የኢትዮጵያውያን ኃላፊነት ነው።

ኢትዮጵያ ዲጂታል ከባቢ እና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የበለጸገ ኅብረተሰብን ለመገንባት የሚያስችላትን አቅም ገና አልፈጠረችም። አቅምን በማጠናከር ስኬታማ ለመሆን ደግሞ ፈጣን ፣ እና ልበ-ሙሉ የተቀናጀ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። አገሪቱ በአሁኑ ወቅት በፈጣን ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ለውጥ ላይ ትገኛለች ። በአገር በቀል የምጣኔ ሀብት ማሻሻያ አጀንዳ እና የአሥር ዓመት ብሔራዊ የልማት ዕቅድ (2011-2022) ጸድቀዋል። እነዚህ ሁሉ የአዳዲስ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ዕድገት ዘላቂ ለማድረግ እና እያንዳንዱ ዜጋ ከአገር አቀፍ ብልጽግና ተጠቃሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ዕድል ይሰጣሉ።

### «ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025» እና «ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን»

ሰነዱ እንደሚያመለክተው፤ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ የአገሪቱን ቁልፍ ዘርፎች ወደ ዲጂታል ሽግግር ለመውሰድ የሚቻልበትን መንገድ የቀየሰ ነው። በጥቅሉ ከዚህ የሚከተለው ዘገባ በ244 ገፅ የተዘጋጀው ስትራቴጂ ያካተታቸውን ቁልፍና ዋና ዋና ጉዳዮች ያስቃኘናል።

ከዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ሰነድ መረዳት እንደሚቻለው፤ ዲጂታል ኢትዮጵያ የዲጂታል ዕድሎችን በመጠቀም ፈጠራ የታከለበትና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል በኢትዮጵያ መንግስት የሚመራ ተነሳሽነት ነው። ከአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ እና የአስር ዓመት የልማት ዕቅድን ከመሳሰሉ ቁልፍ አገራዊ ስትራቴጂዎች ጋር እንዲሁም እንደ አፍሪካ ህብረት አህጉራዊ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ካሉ ዓለም አቀፍ ስትራቴጂዎች ጋር የተሳሰረ መሆኑንም ነው።

ዲጂታል ኢትዮጵያ የመንግሥትን፣ የግሉን ዘርፍና የልማት ኤጀንሲዎች ተዋንያንን በአንድ ላይ በማሰባሰብ፣ መሰረታዊ የዘርፍ ተነሳሽነትን በመለየት የአገሪቱን ዲጂታል ኢኮኖሚ ጉዞ ለማሳለጥ እንዲሁም የኢትዮጵያን የዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን በግንባር ቀደምትነት ለመምራት የሚችሉና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ሊጠቀሙ የሚችሉ አራት ስትራቴጂያዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ዘርፎችን መለየቱን “ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025” ስትራቴጂ ሰነድ በግልፅ ያሳያል።

በዋናነትም ግንባር ቀደም ተብለው ከተለዩት ውስጥ ግብርና፣ የማምረቻ ዘርፍ፣ የመረጃ ቴክኖሎጂና ቱሪዝም ቅድሚያ የተሰጣቸው ዘርፎች መሆናቸውን ይጠቁመናል። ዋና ዋና ጉዳዮችን ለመቃኘት እንዲያመቸን ግንባር ቀደም ተብለው ከተለዩት ውስጥ የተወሰኑትን ከዚህ እንደሚከተለው ለመመልከት እንሞክር።

### ግብርና

በስትራቴጂ ሰነዱ እንደተመለከተው፤ በግብርና ውስጥ የበይነ መረብ ቁሶች አርሶ አደሮች ምርታቸውን እንዲቆጣጠሩ ማስቻል፣ ጥብቅ ሰንሰለት (Block chain) ደግሞ ፍትሃዊ የንግድ ውድድር፣ ደህንነቱ የተጠበቀና የተሻሉ (ርካሽ) የክፍያ አማራጮችን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችላቸው ማድረግ ዋናው የስትራቴጂው ተግባር መሆኑን ይጠቁማል።

ኢትዮጵያን በዚህ ዘርፍ ውጤታማ ለማድረግ ሁለት ምቹ እድሎች መለየታቸውንም ያመለክታል። አንደኛው የዲጂታል ግብርና መድረክን መገንባት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ቴክኖሎጂ መር የሆኑ የግብርና ኢንተርፕራይዞችን (ቴክ-ግብርና) መደገፍና ማበረታታት መሆናቸውን ያብራራል። እነዚህን ሁለት ቁልፍ ጉዳዮች ማቀናጀት ሲቻል የሚፈለገው ውጤታማነት እውን እንደሚሆንም ይተነብያል።

### የማምረቻው ዘርፍ

ሌላኛው ግንባር ቀደም ግብ በዓለም አቀፍ ገበያዎች ተደራሽነትን ለማስፋት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ አዳዲስ የግንኙነት ቴክኖሎጂዎችን መቀበል እና መፍጠር ማስቻል እና ኤክስፖርትን ለማሳደግ በዲጂታል የተደገፉ የሎጂስቲክስ አያያዝ አካሄዶችን ማጎልበት መሆናቸውን ይሄው የስትራቴጂ ሰነድ ያብራራል።

### የመረጃ ቴክኖሎጂ

በዚህ ስትራቴጂ ውስጥ በሶስተኛ ደረጃ ግንባር ቀደም ዘርፍ የሆነው “የመረጃ ቴክኖሎጂ” ነው። ሰነዱ በመረጃ ቴክኖሎጂ አስቻይ የሆነባቸው አገልግሎቶች መገንባትን ይመለከታል። ከዚህ አማራጭ አንጻር በኢትዮጵያ ሁለት መልካም አጋጣሚዎች መለየታቸውን ይጠቁማል። የመጀመሪያው ለባለ ከፍተኛ አቅም እና ተሰጥኦ ማዕከላት መሰረተ ልማት ማቅረብ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ መሪ የንግድ ሥራ ሂደት አቅርቦትን ሊሰቡ የሚችሉና ተሰጥኦ ማሳደጊያ የመረጃ ቴክኖሎጂ ፓርክን ዳግም በማዋቀር በሙሉ አቅሙ ወደ ስራ ማስገባት ነው።

### ቱሪዝም

ቱሪዝምን ተወዳዳሪ ለማድረግ የዲጂታል አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግ ሶስት መልካም አጋጣሚዎች ተለይተዋል። የመጀመሪያው የቱሪዝም ዲጂታላይዜሽን ግብረ ኃይል በማቋቋም የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ዲጂታላይዝ ማድረግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የዲጂታል የገበያ ስርዓትን በማበጀት የቱሪስት ፍሰትን እና የቆይታ እና ተሳትፎ መጠኑን ማሻሻል ነው። ሶስተኛው ደግሞ በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የዲጂታል አገልግሎት እንዲሰጡ አቅማቸውን መገንባት ነው።

### ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ምንድነው?

ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ ነው። በአካል ከሚደረጉ ግንኙነቶች ወጥቶ የዲጂታል አሰራሮችን በመተግበር ወደ ዲጂታል ኢኮኖሚ ለመድረስ ባለ ሂደት ውስጥ ያለ “ጉዞ” ነው። የዲጂታል የሽግግር ጉዞ በመንግስት፣ በንግድ ድርጅቶች እና በማህበረሰቡ መካከል ግንኙነት በአካል ይካሄድ ከነበረበት አናሎግ ህብረተሰብ ወጥቶ ግንኙነትና ልውውጦች በበይነ መረብ በጣም ፈጣን፣ ርካሽ፣ እና ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ወደሚካሄዱበት የተቀናጀና አካታች ዲጂታል ኢኮኖሚ የሚደረግ ጉዞ ነው።

ዲጂታል ኢኮኖሚ የሚያመለክተው የተሻሻለ የኔትወርክ ግንኙነቶችን እና እርስበርስ ተያያዥነት ያላቸውን የዲጂታል መድረኮችን በመጠቀም የሚደረግ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ነው። የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ ከአናሎግ ኢኮኖሚ ይጀምራል። በአናሎግ ኢኮኖሚ ውስጥ በዜጎች በመንግስትና በንግድ ድርጅቶች መካከል ያለው ግንኙነት የዲጂታል ቴክኖሎጂን የማይጠቀም እና በአካል የሚደረግ ነው።

ከአናሎግ ኢኮኖሚ ቀጥሎ የሚገኘው ደግሞ ዝቅተኛ የዲጂታል ተደራሽነት ነው። በዚህ ውስጥ ውስን የዲጂታል መሰረተ ልማት ይኖራል፣ የተወሰኑ የዲጂታል ማሳያዎች ብቅ ብቅ ማለት ይጀምራሉ። የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞው ይቀጥልና አናሎግ ግን የዲጂታል አሰራር እያደገ ይሄዳል። በዚህ ውስጥ አብዛኞቹ አገልግሎቶች አናሎግ የሆኑበት፣ ግልፅ የሆነ የዲጂታል ራዕይ ካልተቀናጁ አገልግሎቶች ጋር ያሉበት እና የሚተገበርበት ነው።

ይህ አናሎግ እና ያልተቀናጀ የዲጂታል አገልግሎት ደግሞ የተቀናጀ የዲጂታል ስርዓትን ይወልዳል። በዚህ ውስጥ የላቀ፣ የተቀናጀ የዲጂታላይዜሽን አገልግሎትና ጠንካራ አስቻይ ስነ ምህዳሮች ይኖራሉ። የዲጂታል ኢኮኖሚም ይገነባል። የዲጂታል ኢኮኖሚ የተሟላ የዲጂታል ኢኮኖሚ የተተገበረበት፣ ከመንግስትና የንግድ ተቋማት ጋር ለመገናኘት የዲጂታል አገልግሎትን የሚጠቀም ነው። የንግድ ተቋማት ፈጠራ የታከለበት አገልግሎት ያቀርባሉ። የመንግስት ስራዎችና አገልግሎቶች ዲጂታል ይሆናሉ። አብዛኞቹ የንግድ መነሻዎች ዲጂታል ይሆናሉ።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## «መንግስቱ የኃይለስላሴን ህገ መንግስት እንደቀደደው፤ መለስ የመንግስቱን እንደቀደደው እኛ አንቀድም ፤ ህጋዊ በሆነ መንገድ እናሻሽለዋለን »

**- ጠቅሳይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ**


ፎቶ፡ ዳኒ አበራ

**ክፍል አራት እና የመጨረሻው**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱላቸው ወቅታዊ አገራዊ ጥያቄዎች ሰፊ ማብራሪያና ምላሽ ሰጥተዋል። ይህንኑ ምላሽና ማብራሪያ በተከታታይ ማስነበባችን ይታወሳል። በዛሬው አራተኛና የመጨረሻው ክፍል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለግንዛቤ ያክል በሚል ለምክር ቤቱ የሰጡትን ተጨማሪ ማብራሪያ ይዘን ቀርበናል።

**ጠቅሳይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፤**

ይቅርታ ! የተከበሩ አፈጉባኤ በቀጥታ ኢንተርፌር ማድረግ ያለብኝ ጉዳይ ባይሆንም አንዳንድ ነገሮችን ግንዛቤ ለማስጨበጥ ትንሽ ጊዜ ልወስድባችሁ ነው።

አንደኛው ይሄ ምክር ቤት የፌዴሬሽን ምክር ቤትን የመገምገም ስልጣን የለውም፣ ቀመር እንዲህ ለምን አላወጣም እንደዚህ አልገመገመም ኢ-ሕገመንግስታዊ ነው፣ ይሄ ምክር ቤት የፌዴሬሽን ምክር ቤትን የመገምገም ስልጣን የለውም፤ ፌዴሬሽን ምክር ቤት የራሱ አሰራር አለው። እናንተ ሕግ ስታወጡ ሕግ የሚታይበት አሰራር አለ፤ እናንተ የምትገመግሙት አስፈፃሚውን፣ ሕግ አውጪውን ሲሆን እነሱን በጋራ ስብሰባዎቻችሁ እነዚህ ጉዳዮች ቢታዩ መጠየቅ ካልቻላችሁ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ተሰብስቦ ስለእናንተ ሕግ አወጣጥ የሚገመግም ከሆነ እኛም እዚህ ተቀምጠን ስለእነሱ የምንገመግም ከሆነ አስቸጋሪ ነው። ማን መልስ ይስጥበት? ፌዴሬሽን ምክር ቤት እዚህ ካለው የሕዝብ ውክልና በላይ በተለየ መንገድ ውክልና ያለው ስብስብ ነው።

እያንዳንዱ ብሔር የተወከለበት ስብስብ ነው። ጥያቄ ካለን በሁለቱ አፈ ጉባዔዎች አማካኝነት የጋራ ስብሰባ አድርገን ባሉበት ይሄን ጉዳይ እንዴት አደረጋችሁት፣ እንዴት አያችሁት ብለን አብራሩ ማለት ነው ያለብን እንጂ እነሱ በሌሉበት የእነሱን አሰራር ትክክል አይደለም ብለን የምንገመግም ከሆነ ቅድም እንዳነሳሁት አይነት ጉዳይ ይፈጠራል። ምክር ቤት ማለት የሁሉ ጠቅላይ ማለት አይደለም፣ የተገለፀ ስልጣን ያለው ሃይል ነው፤ እሱ ታሳቢ ቢደረግ ጥሩ ነው።

ሁለተኛ ከቀመር ጋር ተያይዞ ምክር ቤት ቀመር አላየም የሚለው ስህተት ነው፣ ሕዝብ ቆጠራ ተደርጎ በዚያ መሰረት ሕጉ አልተሻሻለም እንጂ በጣም በርካታ ሪፎርሞች ሰርቷል። ለምሳሌ የጋራ ገቢ፣ የጋራ ገቢ ዛሬና ትናንት አራምባና ቆቦ ነው። ቢሊየን ብሮችን ክልሎች ይወስዳሉ። አሁን ፌዴሬሽን ምክር ቤት አጥንቶ አሻሽሎ የጋራ ገቢ ትክክል አይደለም ብሎ ድሮ ምንም የማያገኙ ክልሎች በሺህ ፐርሰንት፣ በመቶ ፐርሰንት እድገት አግኝተዋል።

ሁለተኛ ቅድም እንዳነሳሁት ክልሎች በቀመሩ ሂሳብ ከፍ ያለ በጀት የሚያገኙ ሁሉም ክልሎች ስላሉበት ተነጋግረው አንዳንድ ክልሎች ከራሳቸው ቀንሰው አነስተኛ ገቢ ላላቸው ተጨማሪ ድጎማ እያደረጉ ነው። እና ምንም አይነት ስራ ሳይሰራ ዝም ብሎ ጅምላ እንደሄደ አድርጎ መውሰድ ትክክል አይደለም። የሕዝብ ቆጠራ ቅድም እንዳነሳሁት አስፈላጊ ነገር ነው።

እንደምታስታውሱት የዛሬ ሁለትና ሦስት ዓመት ገደማ ቆጠራ እንዲካሄድ ወስነን ነበር፣ ቆጠራው እንዳይካሄድ የተቃወማችሁት እናንተ ነበራችሁ፤ አብኖች። በተረጋጋው ጊዜ ማለት ነው።

ጠርተንም አወያይተናችኋል፤ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ፣ ቆጠራው እንዲካሄድ ፍላጎት ነበረ፣ ያላችሁት አይነት መዛባቶች እዚያም እዚያም እንዲስተካከሉ ማለት ነው፣ ቆጠራው ሳይካሄድ ግን ሰው ተነስቶ እንደዚህ ጎደለ፤ እንደዚያ ጎደለ ቢል ንግግር ነው የሚሆነው። ቆጠራውን አካሂደን የጎደለ ነገር ካለ መጠየቅ ግን ያስፈልጋል።

ሁለት ነገር ይነሳል የተከበረው ምክር ቤት በደንብ እንዲያሰምርበት፣ አንደኛው ፍልሰት ነው። ይሄ የክልል ቁጥር ትክክል አይደለም በርካታ ሚሊየን ሰዎች እየፈለሱብኝ ነው የሚሉ ክልሎች አሉ፣ ሰውየው የተቆጠረው እዚያ ነው፤ የሚኖረው ግን እዚህ ነው። ለምሳሌ አዲስ አበባ በሚሊየን የሚቆጠር ፍልሰት አጋጥሞኛል፣ እኔ በጀት የማልሻማው በራሴ ገቢ የማስተዳድረው ለሕዝቤ ነው ግን ከየክልሉ ሰዎች እየፈለሱ ለእነሱ ቤትና ውሃ ማቅረብ ፈተና ሆኖብኛል ክልሎች እየረዱኝ አይደለም ይላል።

ለምሳሌ ኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ ፍልሰት አለብኝ ከደቡብ ክልል ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰው ይፈልስብኛል። ከተለያየ ክልል እንደዚሁ፣ እና ይሄ አልተቆጠረም ለነዚህ ግን አገልግሎት ስጥ እንባላለን ይላሉ። ይሄ ሁሉ የሚፈታው ሲቆጠር ነው፣ ቁጥር ያስፈልጋል፤ ጊዜው ሲስተካከል ተቆጥሮ መስተካከል አለበት ትክክል ነው። ግን በተለየ መንገድ አንዱን ጠቅሞ አንዱን የሚጎዳ አድርጎ ማሰብ አያስፈልግም። ሁሉም በራሱ መንገድ አንዱ በጥቅሙ ተጎድቻለሁ፤ ሌላው በቁጥር ተጎድቻለሁ ይላል ብዙ ሃሳብ ስላለ ማለት ነው።

**ለምሳሌ ኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ ፍልሰት አለብኝ ከደቡብ ክልል ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰው ይፈልስብኛል። ከተለያየ ክልል እንደዚሁ፣ እና ይሄ አልተቆጠረም ለነዚህ ግን አገልግሎት ስጥ እንባላለን ይላሉ። ይሄ ሁሉ የሚፈታው ሲቆጠር ነው፣ ቁጥር ያስፈልጋል፤ ጊዜው ሲስተካከል ተቆጥሮ መስተካከል አለበት ትክክል ነው**

ከአፋር ጋር ተያይዞ የተነሳው አንደኛ አፋር ያለው ቁስለኛ እኛ ነን መድሃኒት የምንሰጠው፣ አፋር የራሱ ደሴት የለውም፤ እኛ ነን የምናክመው ይሄ አደገኛ ልምድ ነው፣ ወለጋ ላይ ውጊያ ስላለብኝ ጦርነት ሁሉ ያለው ወለጋ ነው፣ አፋር ውጊያ ስላለብኝ ጦርነት ሁሉ ያለው አፋር ነው አይነት ዝንባሌ ተው፣ ኢትዮጵያ ሁሉ የታመሰ ነው፣ በቁስለኛ የተሞላ ነው። የፌዴራል መንግስት ለእያንዳንዱ ክልል መድሃኒት ያቀርባል፣ እያንዳንዱን ሆስፒታል በሚችለው ድጋፍ ያደርጋል፣ የአፋርን የተለየ የሚያደርገው ነገር የለም።

ኦሮሚያም እንደዚያ አይነት ስላለ። በዚህ ጉዳይ በየፖሊስ ጣቢያው በየእንትኑ ቁስለኛ አለ፤ እኛ ነን የምናግዘው ባለ አቅም። ክልሎች ግን ለማኝ ሆነዋል፣ ገቢ ማሳደግ ልማት ማምጣት ሳይሆን በቃ የሆነ የሚፈስ ነገር፣ ቅድም እንዳነሳሁላችሁ ገቢያችን ሶስት መቶ ምናምን ቢሊየን ነው፣ 309 ቢሊየን አካባቢ፣ ይሄ አብዛኛውን የሚሄደው ክልል ነው። 379 መንገድ ግንባታ አለ ያልኳችሁ እኮ አንድም አዲስ አበባ ውስጥ የለም፣ ሁሉም መንገድ የሚገነባው ክልል ነው። ሆስፒታል ይገነባል፣ ት/ቤት ይገነባል አብዛኛው ክልል ላይ ነው የሚውለው፣ ግማሹ በእኛ ይሰራል። ግማሹ ደግሞ በእነሱ ማለት ነው።

ኢትዮጵያ መቶ ሁለት መቶ ቢሊየን ዶላር ያስፈልጋታል፣ ከዚህ መቀሌ፣ ከዚህ ባህርዳር፣ ከዚህ አሶሳ፣ ከዚህ ጋምቤላ፣ ከዚህ ሰመራ ሃይዌይ ያስፈልገናል። ባቡር ያስፈልገናል። ሃብቱ ውስን ስለሆነ ነው እንጂ ፍላጎት ስለሌለ አይደለም። ከስር ከስር እየሰራን መሄድ፣ ከስርስር ልማቱ እያደገ ሲሄድ ችግሮች እየተፈቱ እንደሚሄዱ ማሰብ ነው። የኢንፍራስትራክቸር መዛባትን በሚመለከትም እንደተባለው ፌዴሬሽን ምክር ቤት ጥናት አጥንቶ በድርጅትና በካቢኔ ሃሳቡ ቀርቧል፣ ያን ታሳቢ አድርገን ከፍተኛ የመንገድ ችግር ያለባቸውን ክልሎች ምላሽ መቶ በመቶ ሰጥተናል።

አንዱ ክስ ያለው አማራ ክልል ነው፤ ሰፊ የመንገድ ስራ ሰርቷል፣ በኦሮሚያ ምዕራብ ወለጋ ነው፣ በደቡብ ደግሞ አሉ ኮሪደሮች እንደዚሁ ያልተሰሩ፣ ያለፈውን ለመመለስ ተሞክሯል። አሁንም ግን ሰፊ የመንገድ መሰረተ ልማት ያስፈልጋል። ወደ ደቡብ ምዕራብ አዲሱ ክልል ብትሄዱ እኮ ምን አለ መንገድ እኮ የለም፣ ብዙ ስራ ያስፈልጋል። ዞኖች አንዳንዱ ጋር ወረዳ ላይ አስፋልት የለውም፤ የዞን ከተማም አስፋልት የሌላቸው አሉ። እነዚህን ደረጃ በደረጃ እየመለስን ለመሄድ ውስጥ ውስጡን ጥረት እየተደረገ መሆኑን ታሳቢ ማድረግ ጥሩ ነው።

ዘንድሮ ድርቅ በሚመለከት የውጪ እርዳታ ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ውስን ነው። እንኳን የፌዴራል መንግስት እያንዳንዱ ክልል ረድቷል። ሁሉም ክልሎች ረድተዋል ሱማሌም ቦረናንም፣ አፋርንም። አማራ ክልል ይሄ ሁሉ ጣጣ እያለበት ረድቷል ኦሮሚያ ሄዶ። በእርነሱ እርዳታ ጭምር ነው ድርቁን በተወሰነ ደረጃ ለመቋቋም የሞከርነው።

ታክስ ሊሰበስብ ነው መንግስት የሚያስበው ለተባለው እንኳን ከሞተው ካለውም አልተሰበሰበም። የእኛን አካባቢ ችግር አንስተን እንደ አጠቃላይ አገር የምንመራ ሰዎች የምንናገር ካለን ችግር ነው። በአገር ደረጃ ያለውን ነገር

# ወቅታዊ ትንታኔ



ማየት ጥሩ ነው። እንደዚያ አይነት ግንዛቤ ቢወሰድ መልካም ነው።

አፋር ክልል ለምሳሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገንብተናል ባለፈው አንድ አመት ተኩል። ያ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ለአፋር ክልል የተመደበ አልነበረም። ለሌላ ክልል የተመደበ ነው። ከባንክ ጋር ተነጋግረን አፋር ክልል የማይሰራ ከሆነ ይቅርብን ብለን ነው፤ ወደዚያ የወሰድነው። ለምንድነው አፋር ክልል ለፖርት ቅርብ ነው እዚያ ብናመርት ኤክስፖርት ለማድረግ ይመቻል። ምንም አስቻይ ሁኔታ በሌለበት ፕሮጀክቱን በተለመደው አካባቢ መደርደር ትክክልና አዋጭ አይደለም ተብሎ ከሌላ ክልል ተወስዶ ነው አፋር የተመደበው።

አፋር በመንገድ ስርጭት ጥያቄ ሊያነሳ አይችልም። ከሁሉም ክልሎች ከትግራይ ቀጥሎ ሻል ያለ መንገድ ያለው አፋር ነው። ወደ ኤርታሌ የሚሄደው የአስፓልት መንገድ ላይ የፈጀው ሲሚንቶ ሌላ ሶስት እጥፍ አስፓልት ይሰራል። ይሄን ታውቃላችሁ። እኛ የምንፈልገው ፍትሀዊ ልማት እንዲሰራጭ ነው። የተወሰነ ሀብት ተጠቅሞ ሌላው እንዳይጎዳ በተለይ እንደ አማራና ኦሮሚያ ያሉ ክልሎች በየአመቱ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ሲሰበሰብ ከሚያገኙት ገቢ በህጉ ቢገባቸውም እየቀነሱ ለአነስተኛ ክልሎች ይደጉማሉ። ይህን የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት በመጠየቅ ልታረጋግጡ ትችላላችሁ። ፍፁም ነው አይደለም የሚለው አይደለም። ፍጹምነት የለም ስህተት ሊኖር ይችላል ያንን እያስተካከልን እያረቅን እንሄዳለን።

ህገመንግስቱ በአካታች አገራዊ ውይይት ይታይ ያልነው እኮ ችግር ስላለበት ነው። ህገመንግስቱ ግን መንግስቱ የኃይለስላሴ እንደቀደደው፤ መለስ የመንግስቱን እንደቀደደው አንቀድም። ህጋዊ በሆነ መንገድ ግን እናሻሽለዋለን። የመጣው ሁሉ ቢቀድ ስርዓት አይገነባም። ለዚያ ነው አካታች አገራዊ ውይይት ይደረግና በዚያ ላይ ያላችሁን ሀሳብ አንሱ ተወያዩ ሲባል አንወያይም የሚል አካል ህገመንግስት ይላል። ፌዴሬሽን ላይ ባንዲራ እንዲህ መሆን የለበትም የሚል ኢሹ ያነሳል። ሁሉም ያገባኛል የሚል ሁሉ ተወያይቶ ከተስማማን በኋላ ህዝብ የሚወስንበት ዘላቂ ነገር መሰነድ ያስፈልጋል። ያ ሲሆን ነው አገር የሚቀጥለው። ለምንፈልገው ነገር ሲሆን ህገመንግስቱ ሪፈር እናደርጋለን፤ ለማንፈልገው ነገር ሲሆን ደግሞ ህገመንግስቱን አንፈልግም ካልን ያስቸግራል፤ አይሆንም።

ለምሳሌ ወልቃይት፤ ወልቃይት በተመለከተ ባለፈው ፓርላማ ላይ በነበረን ዝግ ውይይት አንድ ባንድ አንስቼላችኋለሁ። አሁን እዚህ አላነሳውም። ወልቃይትን በሚመለከት በተደጋጋሚ አቅጣጫ አስቀምጠናል ለክልሉ። ህግ በተከተለ መንገድ ሶልቭ እንዲደረግ። ለምን መወሰን ቀላል ነው። ከዚያ በኋላ ልጆቻችን እየተባሉ የሚኖሩበትን መንገድ አናድርግ። የፍትህ ጥያቄ ነው የቆየ ጥያቄ ነው። ሁሉም ሰው ህግን ተከትሎ የሚፈታው ጉዳይ ካልሆነ አሁን በደፈናው እንዲህ ነው ብሎ ቢወስን ሁልጊዜ ግጭት ሁልጊዜ መባላት ይፈጠራል። እንደተባለው የተጎዳ ህዝብ የተሰደደ ህዝብ ነው።

ፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው የሚወስነው። ክልሎቹ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባሉ፤ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ጋር ይወያያሉ፤ እዚያ ሲወሰን እኛ እናስፈፅማለን። ወልቃይትን በሚመለከት እስካሁን በትግራይ ክልል ስለነበር በጀት ተመድቧል። አላያችሁም በጀቱን። ህገመንግስታዊ ስለሆነ አምናም ካቻምናም ተመድቦ ነበር። ህገመንግስቱ ለክልሎች መድቡ ይላል። ከተመደበ በኋላ እንዴት እንሰራበታለን ለሚለው በጀት አስተዳደር የሚያየው ጉዳይ ነው።

እኔና እናንተ ግን ትግራይ ችግር ስላለ በጀት አይወሰንም ማለት ግን አንችልም። ቀመሩም አይፈቅድም ህገመንግስቱም አይፈቅድም። አምናም ፀድቆ ነበር ነገር ግን ሊጠቀሙበት አልቻሉም ፈሰስ ተደርጓል። ዘንድሮም ተበጅቷል ችግሩ ከተፈታ የሚጠቀሙበት ይሆናል ካልተፈታ ደግሞ በበጀት አስተዳደር የሚታይ ይሆናል። እንጂ እኛ እዚህ ሆነን የማንፈልገውን ጉዳይ እያፋለስን ከሄድን ትክክል አይደለም። በጀት በሚመለከት ወልቃይት ላይ ችግር አለ። መደገፍ አለበት ወልቃይት። ግን ትግራይ የባሰ ችግር አለ። የትግራይ በጀት ጉዳይ እንዴት ነው የሚሆነው ለምን አትሉም እናንተ። የትግራይ በጀት ጉዳይ የምናነሳው ከቲፒ ኤል ኤፍ መነፅር አንፃር አይደለም።

**እኔና እናንተ ግን ትግራይ ችግር ስላስ በጀት አይወሰንም ማለት ግን አንችልም። ቀመሩም አይፈቅድም ህገመንግስቱም አይፈቅድም። አምናም ፀድቆ ነበር ነገር ግን ሲጠቀሙበት አልቻሉም ፈሰስ ተደርጓል። ዘንድሮም ተበጅቷል ችግሩ ከተፈታ የሚጠቀሙበት ይሆናል ካልተፈታ ደግሞ በበጀት አስተዳደር የሚታይ ይሆናል።**

የትግራይ በጀት የምናነሳው በሕወሓት መነጽር አይደለም፤ ከትግራይ ሕዝብ አንፃር ነው። ቅድም ለትግራዮች እንዴት ትረዳላችሁ የሚል ጥያቄ ተነስቶ ነበር። ግን ያው ትቸዋለሁ፤ የተውኩበት ምክንያት፤ እነዚያ በትግራይ ውስጥ ያለውን ችግር ለመፍታት የሚፍጨረጨሩ ኃይሎች ካሉ ያው ውጤታቸው እየታየ የሚሄድና ሁሉም ዜጋ ሕዝብ በየአካባቢያቸው የሚያግዛቸው ይሆናል በሚል ነው።

ለምሳሌ የአማራ ክልል ከትግራይ ጋር በነበረው ግጭት ጉዳት ደርሶበታል፤ ግን የአማራ ክልል ከትግራይ ተሰደው የመጡ ሰዎች አቅፎ፣ እያበላ ነው ያለው። ትናንት ተዋግታችሁኛልና አትመጡብኝም አላለም። ኑ ወንድሞቼ፤ ፀቤ ከሕወሓት ጋር ነው፤ ከቸገራችሁ ብሎ በአማራ ክልል ጫፍ ጫፍ የሚያበላቸው ሕዝብና መንግሥት ነው። ሕዝቡ እንደሱ ነው።

እና ወልቃይትን በሚመለከት፤ በበጀት አስተዳደር የሚታይ ነገር ካለ፤ ገንዘብ ሚኒስቴር አምናም አይቷል፤ ዘንድሮም ያያል። በተለያዩ ተቋማት ድጋፍ ይደረጋል፤ ግን ለማን ተብሎ ይመደባል ለሚለው ነገር የሚጠፋችሁ አይመስለኝምና በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ክልሎች ሥራቸውን ሰርተው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አቅርበው፤ ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ብንፈጽመው በዘላቂነት ሰላም ሊፈጥር ይችላል በሚል እንጂ የወልቃይት በጀት አንድ ሚሊዮን ሁለት ሚሊዮን እዚህ ቀርቶ እዚያ ቀርቶ ምንም ለውጥ ስለሚያመጣ አይደለም።

ያም ሆኖ ግን በመከላከያ የሚደረግ ድጋፍ እንዳለ የተከበረው ምክር ቤት እንዲገነዘብ ነው። እና በተለየ መንገድ እዚህ አይተን ለመወሰን እንቸገራለን፤ ፌዴሬሽን ተወያይቶ ሕጋዊ መንገድ ሲያስፈጽም ደግሞ እኛ እናስፈጽማለን በሚለው መገንዘብ።

ወልቃይት አካባቢ ኮንሰርን ያደረጋችሁ ሰዎች ሄዳችሁ ምን አቅጣጫ እንደተሰጠ፣ ምን እንደተሰራ፣ ምን እንዳልተሰራ በአካል ብትገመግሙ ጥሩ ነው። እዚህ የሚጠየቅ ብቻ ሳይሆን መሬት ላይ በርካታ ችግሮች ስላሉ። መሬት ላይ ያለውን ችግር አይተን መፍትሔ ብናደርግ አብዛኛው ነገር መስመር የሚይዝ ይመስለኛል።

በዘላቂነት ግን መፍትሔ ማግኘት አለበት፣ ሕዝቡ የተጎዳ ሕዝብ ነው፤ የተሰበረው መመለስ አለበት ያለአግባብ የተበደለው ቢያንስ በሥርዓት እንዲከበር መደረግ አለበት፤ በልማት የደረሰበት ጉዳት ደግሞ ታሳቢ ተደርጎ እንዲሰራ መደረግ አለበት።


ያም ሆኖ ግን ብዙ ቢፈናቀልም፤ ወልቃይት ውስጥ ብዙ የዴሞክራሲ ጥያቄ ቢኖርም ከመሰረተ ልማት አንፃር ደግሞ ብታዩ አንደኛው ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ተጠቃሚ ምዕራብ ትግራይ ነው። ከ320 ኪሎ ሜትር በላይ ኮንክሪት አስፋልት፣ በቀን ሁለት ሦስት መኪና የማይሄድበት አስፋልት አለ አሁን። ጉዳትም አለ፤ የተሰራም ሥራ አለ። ጉዳቱን ጠግነን፣ የተሰራውን ተጠቅመን እንዴት እናለማዋለን የሚለውን እያዩ መሄድ ጠቃሚ ይሆናል ለማለት ነው አመሰግናለሁ !

ማህበራዊ

# ሴቶች

## ቴክኖሎጂን መሰረት አድርገው በሴቶች እየደረሱ ያሉ ጥቃቶችና የጋዜጠኞች ትግል

**ሰላማዊት ውቤ**



ጋዜጠኛ ቅድስት ክፍለዮሐንስ



ጋዜጠኛ ምስራቅ ታረቀኝ



ጋዜጠኛ የሸዋ ማስረሻ



ጋዜጠኛ ማርታ ደጀኔ

ዓለማችንን ከጫፍ እስከ ጫፍ በማገናኘት በአንድ ማዕድ እያቋደሰ የሚገኘው የኢንፎርሜሽንና ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዕድገቱ እጅግ ፈጣን ነው። ለአብነትም በፈረንጆቹ 2019 የወጣ መረጃ መሰረት በዛው ዓመት ከዓለም ሕዝብ ግማሽ ያህሉ የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ መሆኑን ማመልከቱን መጥቀስ ይቻላል። በየሰኮንዱ ብቻ በአማካይ ከ74 እስከ 500ሺ ጂቢ በላይ መረጃዎች ሊላክበት በቅቷል። የማህበራዊ ሚዲያ (ፌስ ቡክ)፤ ቴሌግራም ቲውተርና ሌላውም አጠቃቀሙ ቀላል መሆኑም ተመራጭ ስላደረገው አብዝቶም ግላዊ፣ ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ ፤ የንግድ እና ሌሎች ግንኙነቶች የሚደረግበት ሆኗል። ፍጥነቱና ጠቀሜታውም እየጎላ መጥቷል። ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያየ መገናኛ ብዙሃንና ንግድ ዘርፍ የሚሰሩ ሴቶች እንደሚናገሩት ተግባርን ከማቅለልና ጊዜን ከመቆጠብ ባሻገር ራስን ለማስተዋወቅ፤ ለማንቃትና ለተለያዩ ጉዳዮች ዓይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ተገኝቷል። የጥቅሙን ያህልም ቴክኖሎጂውን መሰረት አድርገው በሴቶች ላይ እየደረሱ ያሉ ጥቃቶች እየተበራከቱ መጥተዋል።

እኤአ በ2020 ወርልድ ዋይድ ዌብ ባጠናው ጥናት ላይ ተሳታፊ የነበሩ 52 በመቶ ወጣት ሴቶችና ልጃገረዶች በይነመረብን በሚጠቀሙበት ወቅት ለወሲባዊ ትንኮሳዎች ለሚያስፈራሩ መልዕክቶች፤ እንዲሁም ግላዊ ፎቶግራፎቻቸው በሌሎች ሰዎች እጅ እንዲገቡ የመደረግ ተገቢ ላልሆኑ የጥቃት ዓይነቶች ተዳርገዋል። 64 በመቶው የዚሁ ጥናት ተሳታፊዎች ደግሞ በድረ ገጽ አማካኝነት ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሌሎች ሴቶችን እንደሚያውቁ የተናገሩበት አግባብ አለ። ከአሥር ሴቶች አንዷ ከ15 ዓመቷ ጀምሮ አንድ የሆነ ዓይነት የሳይበር ጥቃት ይደርስባታል። እንደዚሁም UN Women በፈረንጆቹ 2015 ባደረገው ጥናት ሴቶች ከወንዶች 27 በመቶ በበይነ መረብ (ኢንተርኔት) በተደገፉና ስምና ዝናን ለሚያጎድፉ ጥቃቶች እንደሚጋለጡ ያሳያል።

ሆኖም ‹‹ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም›› እንዲሉ ሴቶች ጥቃቱን ፈርተው ከቴክኖሎጂ ራሳቸውን ማግለል አይገባቸውም ያነጋገርናቸው አንዳንድ ሴቶች አበክረው ሲናገሩ ይደመጣል።

ወጣት ሶሎሜ ይግረም በንግድ ሥራ የተሰማራች ሴት ነጋዴ ስትሆን በሙያዋ ስለ ንግድ ሥራ ሌሎች ነጋዴዎችን በማማከረም ትሰራለች። ሶሎሜ እንደምትለው ዛሬ ሁሉም ነገር በበይነ መረብ (ኢንተርኔት) በቀጥታ ነው የሚከናወነው። ለአብነት በኢትዮጵያ ከሚመደበው አጠቃላይ በጀት 64 በመቶ የሚሆነውን ግዙፍ ድርሻ የሚወስደውን የመንግስት ግዢን ጨምሮ የተለያየ ጨረታ መረጃዎች የሚሞላበትን ሂደት መጥቀስ ይቻላል። በመሆኑም ቴክኖሎጂው እንደ እሷ በንግድ ላይ ለተሰማራች ሴት እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ትናገራለች። በዓለም ላይ የሴትና የወንዶቹ ቁጥር የተመጣጠነ ቢሆንም ከኢኮኖሚው ተጠቃሚ የሆኑት ሴቶች ቁጥር እዚህ ግባ እንደማይባል የምታወሳው ወጣቷ ነጋዴ ቴክኖሎጂው በዓለም ዙሪያ በተለይም በአገራችን በንግዱ ዘርፍ የሚሰማሩ ሴቶች ቁጥርንም ሆነ በመስኩ ያላቸውን ተጠቃሚነት ያሳድጋል ብላ ታምናለች። ግን ደግሞ ሴቶች ሲጠቀሙ ለተለያዩ ጥቃቶች እንዳይጋለጡ እጅግ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ትመክራለች። ይሄን የቀጥታ (ኦን ላይን) ጨረታ አዘወትረው ወንዶችም በክፍያ ይሞሉላቸዋል የምትለው ሶሎሜ ራሳቸውን ችለው መሙላት እንዳለባቸውና ከዚሁ ጋር በተያያዘ በኦን ላይ ከወንዶች ሊገጥማቸው የሚችለውን የጥቅም ግጭት ጫናን ተቋቁሞ በአሸናፊነት ለመውጣት እና አጠቃቀምን ጥንቃቄ የተሞላበትና ውጤታማ ለማድረግ ከቴክኖሎጂው አንዳንዶቹ ላይ ምን አልባት በዙሪያው ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ስልጠና መውሰድ ሊያስፈልግ ሁሉ እንደሚችልም ትጠቁማለች።

የትኞቹም ዓይነትና በየትኛው ደረጃ ያሉ ሴቶች በመስኩ የሚያደርጉትን ተሳትፎ ራስን የበለጠ ከማሳደግና ተጠቃሚ ከማድረግ ጋር የምታያይዘው ጋዜጠኛ ቅድስት ክፍለዮሐንስም እንደምትለው በማህበራዊ ሚዲያ (ፌስ ቡክም) ሆነ በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች የአንዲት ሴትን ራቁት ገላ እንዲሁም በወሲብ ድርጊት እየተሳተፈች እንደሆነች የሚያሳይ ምስል በመልቀቅ ሴቶች ላይ ጥቃት ይደርሳል። የሚገርመውና እጅግ የሚያሳዝነው ጥቃት ፈፃሚዎቹ በቀል በሚመስል ሁኔታ ተጠቂዋ የት እንደምትኖር የግል መረጃዎቿ ጭምር ከምስሉ ጋር የሚሰራጭበት ሁኔታ መኖሩን በተደጋጋሚ መታዘቧን ትናገራለች። ይሄ ዓይነቱ ጥቃት በተጠቂዋ፤ ብሎም በወንድም ሆነ ሴት ጓደኞቿ፤ እንዲሁም በልጆቿና በቤተሰቧ ስነ ልቦና ላይ የሚያሳድረው ጫና ቀላል አይደለም የምትለው ጋዜጠኛ ቅድስት ብዙ ጊዜ በዚሁ ጥቃት ፍራቻ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ንቁ የቴክኖሎጂው ተሳታፊ ሴቶች ራሳቸውን ከቴክኖሎጂው ተጠቃሚነት ሲያገሉ ማየቷን ታወሳለች።

ስም ማጥፋትና የሐሰት አርትኦት በቴክኖሎጂው አማካኝነት በሴቶች ላይ ከሚደርሱ ጥቃቶች የሚደመር መሆኑንም ትጠቅሳለች። በቅርቡ ቴክኖሎጂን መሰረት አድርገው እየደረሱ ያሉ ጥቃቶችን ለሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶች ለማሳወቅና ለመከላከል በተዘጋጀና በተካፈለችበት ስልጠና በሀሰት ማንነት አርትዖት በእውነተኛ የምስሉ ባለቤት ሴት ላይ የተለያየ ተፅዕኖ መፍጠሩን ያየችበትም አጋጣሚ ትናገራለች። የዚችን ሴት እውነተኛ ፊቷን ብቻ በመውሰድና ከሌላ የወሲብ ፊልም ጋር በማቀናጀት ራቁቷን እንደሆነች ወደሚያሳይ ቪዲዮ መለወጡን ተረድታለች። ይሄ ደግሞ አሁን ላይ በቴክኖሎጂው በስፋት እየተሳተፉ ያሉትን ብቻ ሳይሆን ወደፊት ለመሳተፍ የሚያስቡትን በመገደብ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደሚያደርስ ከወዲሁ መገመት እንደሚቻልም ታነሳለች።

በአብዛኛው እንዲህ ዓይነት ጾታዊ ጥቃቶች የሚሰነዘሩት በቴክኖሎጂው ንቁ ተሳታፊ በሆኑ ሴቶች ላይ ነው። እነዚህ ሴቶች በታዋቂ መገናኛ ብዙሃን ወይም በሌላ ተቋም የሚሰሩና ታዋቂዎችም ሊሆኑ ይችላሉ ስትል አስተያየቷን የሰጠችን የቃና ቲቪ ወጣት ጋዜጠኛ ምስራቅ ታረቀኝ ነች ። የዚህ ጥቃት መነሻ ምክንያት በቀልም ሆነ ምንም ዓላማው ሴቶች በስፋት በቴክኖሎጂው እንዳይሳተፉ መገደብ እንደሆነም ታነሳለች ።

እንዳለችው በተለይ በቴሌቪዥን መስኮት ሆነ በሌላ ምስላቸው እየታየ ሥራቸውን የሚሰሩ ሴቶች ይበልጥ ለጥቃቱ ተጋላጭ የሚሆኑበት አጋጣሚ የጎላ ነውም ትላለች። ማናቸውም ቴክኖሎጂን በመጠቀም ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንደማናቸውም ዓይነት ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች የሴቶችን መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች እንዲሁም ክብራቸውንና እኩልነታቸውን ይጥሳሉ። እኩል ተጠቃሚነታቸውን በማስተጓጎልም እያንሰራራ ያለ ዕድገታቸውን ወደ ኋላ ይጎትታሉ። በሁሉም ደረጃ በሕይወታቸው ላይ ከፍተኛም ተፅዕኖ እንደሚኖራቸው አያጠያይቅም። በስነ ልቦና ላይ የሚያሳድሩት ጫናም ቢሆን ቀላል አይሆንም። በኬኒያ፣ ዴሞክራቲክ ኮንጎ ሜክሲኮ ፤ ቦስኒያን ጨምሮ በሰባት አገራት የተካሄደን አንድ ጥናት ዋቢ አድርጋ ጋዜጠኛዋ እንደተናገረችው በነዚህ አገራት ከሚኖሩ ሴቶች መካከል በቴክኖሎጂ በመደገፍ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ሰለባ የሆኑ አሉ። በጥቃቶቹ በማያቋርጥ ጭንቀት፤ ድብርት፤ የአእምሮና የስሜት ውጥረት ተከታታይ ችግር ውስጥ የገቡበት ሁኔታ መኖሩን ጥናቱ እንደሚያመላክት ወጣቷ ጋዜጠኛ ምስራቅ ታወሳለች። በሴቶች ላይ የሚደርሱ ትንኮሳዎች ከማህበራዊ (ፌስ ቡክ) ገጽ ውጭ በኢሜል በሀሰተኛ ኢሜል መለያ አማካኝነት ተለጥፈው ብዙ ችግሮች ያደርሳሉም ትላለች። ጭራሽ አንዳንድ ሴቶች በወሲባዊ ድርጊት ወቅት በቪዲዮ እየተቀረፁ እንደሆነ በማያውቁበት ሁኔታ ተቀርፀው በበየነ መረብ የሚሰራጭበት አስከፊ ጥቃት የሚደርስባቸው ሁኔታም እንዳለ ትናገራለች።

ምስራቅ ጥቃቱ የሚደርስባቸውን ሴቶች ዓይነት አስመልክታም የአመነስቲ ኢንተርናሽናል ተመራማሪዎችን ዋቢ ያደረገ ሀሳቧን በማካፈል ነው አስተያየቷን የቋጨችው። እንደምትለው ታዲያ ተመራማሪዎቹ እንዳረጋገጡት በአሜሪካና በእንግሊዝ ያሉ ሴት ጋዜጠኞች እና ፖለቲከኞች በበየነ መረብ ላይ የጥቃት ሰለባ የመሆን ዕድላቸው ከነጭ አቻዎቻቸው ጋር ሲነፃፀር 84 በመቶ ከፍ ያለ ነው። ጥቁሮችና ከአናሳ ጎሳ የሆኑ ሴቶች 34 በመቶ የበለጠ በተሳዳቢዎች ወይም ችግር በሚፈጥሩ ትዊቶች ውስጥ የመጠቀስ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።

አካል ጉዳተኞች ከጉዳት አልባው የሕብረተሰብ ክፍል በበለጠ በቴክኖሎጂው አማካኝነት የሚደርስ ጥቃት ተጋላጭ ናቸው ያለችን ደግሞ ጤና እና ስነ ተዋልዶ ላይ ትኩረት በማድረግ በግል ሥራ የምትተዳደረው ጋዜጠኛ ማርታ ደጀኔ ነች።

እንደ ማርታ ዲጂታል ሚዲያው ለአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚና ተሳታፊ የሚሆኑበት ሰፊ ዕድል ይዞ መምጣቱን የምታስታውሰው ማርታ በተለይ ሴት አካል ጉዳተኞች አሁንም በዕድሉ የበለጠ በመጠቀምና ተሳትፏቸውን በማጠናከር የራሳቸውን ችግር ከመፍታት ጀምሮ በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን የድርሻቸውን ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል። የአካል ጉዳት የሌለባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በፊናቸው አካል ጉዳተኛውን የማገዝ፤ የማስተዋወቅ፤ የማዝናናት፤ የማስተማር ሥራ በማከናወን በአመለካከት ላይ ፈር ቀዳጅ መሆን ይገባቸዋል።

ጋዜጠኛ ኪያ አሊን በጉዳዩ ዙሪያ በተዘጋጀ አንድ መድረክ ላይ ለሙያ አጋሮቿ ጥናቶችን መሰረት ያደረገ ግንዛቤ ስታስጨብጥ ነው ያገኘናት። ጋዜጠኛዋ እንደምትለው ቴክኖሎጂው አዎንታዊም አሉታዊም ጎኖች አሉት። ራስን ለማስተዋወቅና ለማንቃት ብሎም ከአንዱ የዓለም ጫፍ ወደ ሌላው የዓለም ጫፍ መረጃን በቀላሉና በፍጥነት ለመለዋወጥም ሆነ ለማስተላለፍ ማገዙ፤ ሴቶችም በስፋት የዚሁ ዕድል ተቋዳሽ መሆናቸው አያጠያይቅም። ሆኖም ቴክኖሎጂውን መሰረት አድርገው በሴቶች ላይ እየደረሱ ያሉ ጾታዊ ጥቃቶች እንዳሉ የተለያዩ ሴቶች ሲናገሩ ይደመጣሉ። ከነዚህም መካከል የማስፈራራትና የመበደል፤ ለአንዲት ሴት ተገቢ ያልሆነ እና ያልተፈለገ ትኩረት በመስጠት መከታተልና ማስጨነቅ እንዲሁም ከወሲብ ጋር የተያያዘ ባህርይን የሚያሳዩ ወሲባዊ ትንኮሳዎች ይጠቀሳሉ።

በተለይ የብልግና ስዕሎችን በሚያሳዩ መጽሔቶችና ድህረ ገጾች ጣቢያዎች በአጠቃላይ በኢንተርኔት ዌብ ወሲባዊ ትንኮሳዎች የተለመዱና ሴቶች በመስኩ ለሚያደርጉት የነቃ ተሳትፎ ስጋት መሆናቸውን ኪያ ትናገራለች።

በኢትዮጵያ ሴት ጋዜጠኞች ማህበር የሥራ አስፈፃሚ አባል ጋዜጠኛ የሸዋ ማስረሻ እንደምትለው በመገናኛ ብዙሃን ዘርፉ የተሰማሩትም ሆኑ ሌሎቹ ሴቶች ላይ በቴክኖሎጂው አማካኝነት ከሚደርሱ ጥቃቶች ድብቅ በሆኑ የማህበራዊ ሚዲያ (ፌስ ቡክ) ና የተለያዩ አካውንቶች መተቸት ይጠቀሳል። ትችቱ ደረቅ ሳይሆን ማስፈራርያ፤ ስድብና ስም ማጉደፍና ሥራዎቻቸውን ማጠልሸት የተቀላቀለበት ነው። እነዚህ አጠልሺ ነገሮች በማያውቁበት ሁኔታ የገዛ አካውንታቸውን ሀክ በማድረግ የሚለጠፉበት ሁኔታም ይስተዋላል። አንዳንዶቹ በተደራጀ ቡድን የሚደረጉ ጥቃቶች ናቸው። ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ሴት ጋዜጠኞች ለዚህ ጥቃት በመዳረግ እየተሰቃዩ መሆናቸውም ማህበሩና አንዳንድ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚያደርጉት ጥናት ታይቷል። ጥቃቶቹ የሴቶችን የጾታ እኩልነት ለማረጋገጥም ተግዳሮት መሆናቸው ተመላክቷል። ጥቃቶቹ ድንበር የለሽ እንደመሆናቸው በቤተሰብ፤ በማሕበረሰብ፤ በሥራ ቦታዎች፣ በመዝናኛ ብዙሃን፤ በፖለቲካ፤ በስፖርት፤ በጤና አገልግሎቶች በትምህርት ሁነቶችና በሌሎች ሲደርሱ ይስተዋላሉ።

ግን ደግሞ በቴክኖሎጂው መስክ በተለይም በአገራችን እንዲህ ዓይነቱን ሴቶች ላይ የሚሰነዘር ጥቃት በሕግ አግባብ ዳኝቶ መፍትሄ እንዲያገኝ የሚደረግበት አግባብ እጅግ ጠባብ ነው። ሆኖም ጥቃቱን የሚመክቱ ህጎች አሉ። ያውም ደግሞ የበየነ መረብ አገልግሎት ገና ሳይጀመረ የነበሩ በርካታ ሕጎች ናቸው። ለምሳሌ፡- የተባበሩት መንግስታት አብዛኞቹ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ሲዘጋጁም ሆነ ወደ ትግበራ ሲገቡ እንዴውም የበየነ መረብ አገልግሎት አልተጀመረም። በተለይም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የህፃናት መብቶች ስምምነትም (CRC)ም ሆነ በሴቶች ላይ የሚደረግ መድልዎ የማስወገድ ስምምነት (CEDAW) ም እንዲሁ። እነዚህ ሰነዶች ለልጃገረዶችና ለወጣት ሴቶች ጥበቃና ከለላ የሚሰጡ ማዕቀፎች ሲሆኑ ሴቶች መሰረታዊ መብቶቻቸውን በመጠበቅ ረገድ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ ይደነግጋሉ የምትለው የማህበሩ ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ አባል ጋዜጠኛ የሸዋ ማስረሻ እነዚህ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች የተዘጋጁት የበየነ መረብ አገልግሎት በዓለማችን ላይ ባልነበረበት ዘመን መሆኑንም ታስረዳለች። አሁን ላይ ማህበሩ እነዚህን ሕጎች መሰረት አድርጎ አባላቱን በቴክኖሎጂው አማካኝነት ከሚደርስ ጥቃቶች ለመከላከል ከተለያዩ አካላት ጋር እየሰራ ይገኛልም ብላለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

ያለንበት ወቅት ከባዱ የክረምት ወር መጀመሪያ ሐምሌ እንደመሆኑ ማልዶ ከሚጥለው ዝናብ በተጨማሪ ጭፍጋጋ ቀናትን እያሳለፍን እንገኛለን።በዛሬው የአዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችንም ከክረምት ጋር ጥምረት ያላቸውን አደጋ ነክ ዜናዎች ባለፉት ዘመናት በአገራችን እንዴት እንደነበሩ ለማየት ሞክረናል።ሌሎች ዘገባዎችን ጨምሮ ከሕገወጥ እርድ ጋር በተያያዘም በመዲናችን ይታዩ የነበሩ ችግሮች የተዘገቡባቸውን ጋዜጦች ይዘናል፡፡

**በዝናም ምክንያት ተራራ ተንዶ ስለሞቱት ሰዎችና ከብቶች**

በአርሲ ጠቅላይ ግዛት በከንባታ አውራጃ በዴንሳ ጥምባሮ ምክትል ወረዳ ግዛት በአቶ ፀደቀ ጋረዴ ባላባትነት ውስጥ በነሐሴ 24 ቀን 1946 ዓም ለ25 አጥቢያ ሌሊቱን በዘነበው ኃይለኛ ዝናም በሣና የተባለው ተራራ ተንዶ፤ ከዚሁ ጋራ ሥር የሚኖሩ የቤቱ ጌታ አንቃሞ፣ 2ኛ ሚስቱ በቦሬ በዶሬን፣ 3ኛ ልጁን ሽከሜ አንቃሞ የሚባሉትን ሰዎችና ከበረት የነበሩት ፲፩ የቀንድ ከብቶች፤ ሁለት ባዝራ ፈረሶች፣ ፰ በጎች በናዳው የጋራ አደጋ ሲሞቱ፤ አንደ ዶሮና አንድ ባዝራ ፈረስ ከዚሁ አደጋ ድነው ታይተዋል።ከተናደው ጋራ ሥር አንድ ምንጭ ፈንድቶ መታየቱን ያውቁት ዘንድ እገልፅሎታለሁ፡፡

**ማህተም የአርሲ ጠቅላይ ግዛት ፖሊስ ዋና ጽ/ቤት ፡ ፡**

**ፊርማ ሻለቃ አበበ ወልደ ሥላሴ የአሩሲ ጠቅላይ ግዛት ፖሊስ ምክትል ዋና አዛዥ**

**(ነሐሴ 27 ቀን 1946 የወጣው አዲስ ዘመን)**

**የነፋስ አደጋ**

ጎንደር፤ (ኢ-ዜ-አ) በጎንደር አውራጃ ግዛት በታች አርማጭሆ ወረዳ በአፍደራፊ ከፍተኛና አካባቢው ባለፈው ረቡዕ ዝናም ቀላቅሎ የነፈሰው ኃይለኛ ነፋስ በንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱን ተገለጠ፡፡

በዚሁ የነፋስ አደጋ የ፳፬ መኖሪያ ቤቶች የቆርቆሮ ክዳን ተገነጣጥሎ ከጥቅም ውጪ ሆኗል።እንዲሁም የእመት ታደለች ገብረሕይወት አንድ ክፍል የመኖሪያ ቤት በቤት ውስጥ ካለው ምድጃ ላይ በነፋስ ኃይል በተነሳው እሳት ተቃጥሏል፡፡

ይኸው የነፋስ አደጋ በንብረት ላይ ካደረሰው ጉዳት ሌላ በሰው ሕይወት ላይ አደጋ አለማድረሱን፤ ምክትል የመቶ አለቃ ግርማ ዘውገ የበጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ፖሊስ የማስታወቂያና ሕግ ክፍል ሹም ገልጠዋል፡፡

**(ሰኔ 14 ቀን 1964 ዓ.ም የወጣው አዲስ ዘመን)**

**የተማሪዎች ልብስ በሽያጭ ታደለ**

ከጅማ፤ የትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር በትምህርት ገበታ ላይ የሚውሉት ሕፃናትና ጎልማሶች እንደየ ትምህርት ደረጃቸው የመለያ ልብስ እንዲለብሱ ባደረገው ውሳኔ መሠረት ለከፋ ጠቅላይ ግዛት ትምህርት ቤቶች ማለት ለአንደኛ ለ፪ኛ ደረጃ ተማሪዎች ፩ሺህ ፫፻፹፬፤ ፪ኛ ለአንደኛና ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፫፻፲፮ በድምሩ ፬ ሺህ ፩፻ ተማሪዎች በሽያጭ የሚታደል ልብስ ሰኔ ፲፰ ቀን ፶፯ ዓ.ም ከአዲስ አበባ ተልኮ ሲታደል የዋለ መሆኑን የጠቅላይ ግዛቱ ትምህርት ቤቶች ጠቅላይ ሥራ አስኪጅ አቶ ስዩም ወ/መስቀል ገልጠዋል፡፡

በዚህ ዓመት በጠቅላይ ግዛት በሚገኙት ፲፰ ትምህርት ቤቶች እስከ ፮ኛ ክፍል ድረስ የሚሰጠውን ትምህርት ሲከታተሉ የቆዩት ፩፻፵ ወንዶችና ፳፩ ልጃገረዶች ተማሪዎች ከሰኔ ፲፯ ቀን ጀምሮ ወደ ፱ ክፍል ማለፊያ ፈተና እንደሚቀበሉ ታውቋል፡፡

**(ሰኔ 18 ቀን 19 57 የወጣው አዲስ ዘመን)**

**የሕዝባዊት ቻይና ኤክስፐርቶች አዲስ አበባ ገቡ**

አዲስ አበባ፤ (ኢ-ዜ-አ-) ሰባት የኮሚኒስት ቻይና መንግሥት የጠቅላይ ግዛት ከተማዎች፤ የኤሌክትሪክ ጥናት አዋቂዎች፤ በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ከተማዎች የሚቋቋሙትን የኤሌክትሪክ መብራቶችን ጥናት ለመመልከት ጧት በአይሮፕላን ከፔኪንግ አዲስ አበባ ገቡ፡፡

በሚስተር ማ-ሚንግ-ቲ- የሚመሩት ሰባቱ አዋቂዎች የዲዘልና በወሀ ጉልበት የሚሠራ የኤሌክትሪክ ኃይል መስጫ መሣሪያዎች ኢንጂነሮች ናቸው፡፡

እንግዶቹ በኢትዮጵያ ውስጥ በልዩ ልዩ ጠቅላይ ግዛቶች የኤሌክትሪክ መብራት የሚቋቋምባቸውን ሥፍራዎች እየተዘዋወሩ እንዲመለከቱ የላካቸው የቻይና የውጪ አገር የኤኮኖሚ ኅብረት ሚኒስቴር ነው፡፡

ከዚህ ቀደም የቻይና የመንገድ ቅየሳና የወሀ ልማት ኤክስፐርቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው አሁን በጥናት ላይ እንደሚገኙ መገለጡ የሚታወስ ነው፡፡

**(ሐምሌ 1 ቀን 1964 ዓ.ም የወጣው አዲስ ዘመን)**

**ያለፈቃድ የታረዱ ፩፻፴፯ በጎች**

**ለእግዚቢት ተይዘዋል**

በአዲስ አበባ በልዩ ልዩ ሠፈሮች ያለፈቃድ የታረዱ ፳፰ በጎች፣ አንድ ጥጃና ፩፻፴፯ የበግ ጭንቅላቶች ትናንት መያዛቸውን ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ጽዳት ክፍል የተገኘው ወሬ ያስረዳል፡፡

ሕገወጥ ተግባር ሲፈጽሙ የተገኙት ሰባት ሰዎች ከነኤግዚቢቱ የያዙ የጽዳት ክፍሉ ያሠማራቸው ፬ የሚሆኑ የጽዳት ዘበኞችና ሠራተኞች ናቸው።ያለ ፈቃድ ታርደው ከተገኙት ውስጥ ጥጃው ከሞተ በኋላ ለበላተኛ ለሆቴል ምግብ ሆኖ እንዲያገለግል የተደረገ መሆኑ ታውቋል።ይህንን ተግባር የፈጸመው ሰው አብሮ ተይዟል።

የፅዳቱ ክፍል ዋና ዲሬክተር የተያዙት ሥጋዎች ከፍርድ ቤት ከቀረቡ በኋላ ቈራ ተወስደው እንዲቃጠሉና አራጆቹ እንዲቀጡ ትዕዛዝ ሰጥተዋል።ባለፈው ጊዜ ፩፻፹፯ የበግ ጭንቅላት ሥጋና ቆዳ ተይዘው መቃጠላቸው የሚታወስ ነው፡፡

የፅዳት ክፍሉ ሠራተኞች የሚያደርጉትን ጥብቅ ቁጥጥር እየተቃወሙ አምባጓሮ የሚያበቅሉ ብዙ ሰዎች መኖራቸው ተገልጧል።ይህንን አድራጎት የሚከታተሉ ሕገወጦች የወገኖቻቸው ጤና እንዳይጠበቅ የሚጥሩ ናቸው፡፡

አድራጎታቸው ሁሉ ከሕግ የወጣ ስለሆነ፤ በግሣፄ ብቻ መታለፍ የለባቸውም።ዐጥፊዎቹ በሕግ ፊት ቀርበው ቅጣት እስኪፈጸምባቸው ድረስ የጽዳት ዘበኞቹ ከርኅራኄ የወጣ ተግባር ባይፈጽሙ መልካም ነው፡፡

**(ሰኔ 11 ቀን 1957 የወጣው አዲስ ዘመን)**

# ዓለም አቀፍ

## በሺንዞ አቤ ግድያ ወቅት የጥበቃ ክፍተት እንደነበረ የጃፓን ፖሊስ አመነ

የጃፓን ፖሊስ ባለፈው ዓርብ በደቡባዊቷ ናራ ከተማ የቀድሞው የጃፓን ጠቅላይ ሚኒስትር ሺንዞ አቤ ግድያ በተፈጸመበት ወቅት የፀጥታ ጥበቃ ክፍተቶች እንደነበሩ አመነ። የናራ ፖሊስ አዛዥ ቶሞአኪ ኦኒዙካ “በፀጥታ አጠባበቁ ላይ ችግሮች እንደነበሩ መካድ አይቻልም” ብለዋል።

ሟቹ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሺንዞ አቤ ለጃፓን የላይኛው ምክር ቤት የሚወዳደር ዕጩን ወክለው ቅስቀሳ በሚያደርጉበት ወቅት በተተኮሰባቸው ጥይት ሕይወታቸው ማለፉ ጃፓንን ብሎም በመላው ዓለም ድንጋጤን ፈጥሯል። ሺንዞ አቤ ቅስቀሳ ሲያደርጉበት የነበረው የምክር ቤት ምርጫ ቀድሞ በታቀደው መሠረት ዕሁድ ዕለት ተካሂዷል።

የምርጫው ትንበያ እንደሚያሳየው ሺንዞ አቤ ሲቀሰቅሱለት የነበረው እና ከፍተኛ ተደማጭነት ያለው የገዢው ሊበራል ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኤልዲፒ) እንዲሁም ጥምር አጋሩ ኮሜይቶ አብላጫውን ድምጽ ያገኛሉ ተብሎ ይገመታል። በአቤ ላይ ግድያውን በመፈጸም የተጠረጠረው የ41 ዓመቱ ቴሱያ ያማጋሚ አንድ በስም ያልተጠቀሰ ተቋም ላይ ቂም ይዞ ነበር ሲል ፖሊስ ይፋ አድርጓል።

የጃፓን መገናኛ ብዙኃን ለምርመራው ቅርብ የሆኑ ምንጮችን ጠቅሶ እንደዘገቡት ከሆነ ተጠርጣሪው ወላጅ እናቱን የገንዘብ ቀውስ ውስጥ ከከተተ አንድ የሃይማኖት ቡድን ጋር ሺንዞ አቤ ግንኙነት እንዳላቸው ብሎ ያምናል። ፖሊስ አክሎም ተጠርጣሪው በቤት ውስጥ በተሰራ ሽጉጥ ተጠቅሞ ወደ ሺንዞ አቤ ላይ መተኮሱን ማመኑን ተናግሯል።

“ለእኛ አስቸኳዩ ጉዳይ ምን እንደተፈጠረ ለማብራራት ጥልቅ ምርመራ ማካሄድ ነው” ያሉት የፖሊስ አዛዡ ኦኒዙካ፤ ተፈጥረዋል ያሏቸውን ክፍተቶች የት ላይ እንደሆኑ ከመግለጽ ተቆጥበዋል። ተጠርጣሪው ያማጋሚ በጃፓን የባሕር ኃይል ውስጥ ለሦስት ዓመታት ማገልገሉን ለፖሊስ መናገሩም ተገልጿል። በቅርቡ ደግሞ በምዕራብ ጃፓን በሚገኝ ፋብሪካ ውስጥ ሲሰራ ነበረ ተብሏል።

አቤ ሕይወታቸው ያለፈበት ጥቃት የተፈጸመባቸው ከዋና ከተማዋ ቶኪዮ በስተደቡብ 480 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ናራ ከተማ ውስጥ በሚካሄድ የምክር



ቤት ምርጫ ቅስቀሳ ላይ ንግግር ሲያደርጉ ነበር። አቤ በጥይት ከተመቱ በኋላ ወዲያውኑ መሬት ላይ የወደቁ ሲሆን፣ በፍጥነት ወደ ህክምና ቢወሰዱም ሕይወታቸውን ማትረፍ አለመቻሉን የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

## የአውሮፕላን ቲኬት ዋጋ«ያስጥርጥር» የበለጠ መጨመሩ አይቀርም ተባለ

የአየር ጉዞ ቲኬቶች “ያለጥርጥር” ዋጋቸው መጨመሩ አይቀርም ሲሉ የዓለም አቀፉ የአየር ትራንስፖርት ማኅበር ዳይሬክተር ጄኔራል አሳሰቡ። የቀድሞ የብሪቲሽ ኤየርዌይስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት ዊሊ ዎልሽ፤ ኮቪድ ካስከተላቸው ጫናዎች መላቀቅ ጀምሮ የነበረው ዘርፉ፣ በነዳጅ ዋጋ ጭማሪ እንዲሁም የሩሲያ እና የዩክሬን ጦርነት የአውሮፕላን ቲኬት ዋጋ እንዲጨመር ያደርጋል ብለዋል።

ዎልሽ ተጓዦች የአውሮፕላን ቲኬት ዋጋ እንደሚጨምር ከግምት በማስገባት ለጭማሪው ዝግጁ መሆን አለባቸው ሲሉም አሳስበዋል። “ለተጓዦች የአውሮፕላን ቲኬት ዋጋ የበለጠ ውድ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም” ብለዋል። ለአየር ጉዞ ዋጋ መጨመር ዋነኛ ምክንያቱ ደግሞ የነዳጅ ዋጋ መጨመሩ መሆኑን አመልክተዋል።

“ከፍተኛው የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ፤ የቲኬት ዋጋ



ጭማሪ ላይ ይንጸባረቃል” ብለዋል። ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምጣኔ ሃብታቸው እያገገመ በነበሩ አገራት ላይ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ እያሳየ ይገኛል። የሩሲያ እና የዩክሬን ጦርነት ደግሞ የበለጠ ነዳጅ እንዲወደድ ምክንያት ሆኗል።

ምዕራባውያን በሩሲያን ነዳጅ ላይ እቀባ እየጣሉ ነው። አሜሪካ ሙሉ በሙሉ ከሩሲያ ነዳጅ ማስገባት እንደምታቆም ይፋ አድርጋለች። የአውሮፓ ኅብረት ደግሞ በእአአ 2022 ማጠናቀቂያ ላይ ከሩሲያ ወደ ኅብረቱ አገራት የሚገባው የነዳጅ መጠንን ዜሮ እንደሚያደርግ አስታውቋል።

የሩሲያ ነዳጅ ከገበያ እንዲወጣ መደረጉ በሌሎች ነዳጅ አምራቾች በኩል ለገበያ የሚቀርበውን የነዳጅ ዋጋ ከፍ እንዲል ያደርጋል። ዎልሽ እንደሚሉት ከሆነ የአየር መንገዶች ከፍተኛው ወጪ ነዳጅ ነው። “ከፍተኛ የነዳጅ ዋጋ ተጓዦች ለአየር ትኬታቸው ከፍተኛ ገንዘብ እንዲከፍሉ ማስገደዱ የሚቀር አይደለም” ሲሉ የዓለም አቀፉ የአየር ትራንስፖርት ማኅበር ዳይሬክተር ጄኔራል ዊሊ ዎልሽ መናገራቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

# ማክሰኞ ስፖርት

አዲስ ዘመን

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## በዓለም ቻምፒዮና የሚሳተፈው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቡድን ወደ ኦሪጎን ጉዞውን ጀምሯል

ብርሃን ፈይሳ

በሩጫ፣ ዝላይ እና ውርወራ ስፖርቶች ምርጥ አትሌቶች ብቃታቸውን ለማሳየት የሚፋለሙበት የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና በተያዘው ሳምንት መጨረሻ ይጀመራል። በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ለአንድ ዓመት ተራዝሞ የቆየው ይህ ውድድር፤ የ192 አገራት ብሄራዊ ቡድኖች ውስጥ የተካተቱ 1ሺ900 የሚሆኑ አትሌቶች ተሳታፊ ይሆኑበታል። ለአስር ቀናት በሚቆየው ውድድር የሚካፈሉ አገራትም ብሄራዊ ቡድኖቻቸውን ወደስፍራው በማጓጓዝ ላይ ይገኛሉ።

ከእነዚህ መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ስትሆን የመጀመሪያ የአትሌቲክስ ብሄራዊ ቡድኗ አባላት ትናንት ከምሽቱ 4ሰዓት ከ30 ላይ ወደ ስፍራው አቅንተዋል። በአምስት ዙር ተከፋፍሎ ወደ አሜሪካዋ ኦሪጎን የሚጓዘው ቡድን ዛሬ ምሽትን ጨምሮ በቀጣዮቹ ቀናት ወደ ስፍራው እንደሚያመራም ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የተገኘው መረጃ ያመላክታል። ከመጀመሪያው ጀምሮ በዚህ ውድድር ላይ ተካፋይ በመሆን በሜዳሊያ ሰንጠረዥ ላይም ስሟን ማስፈር የቻለችው ኢትዮጵያ በ18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ላይ አዳዲስና ነባር አትሌቶችን ያሰባጠረ 47 አባላቱን ጨምሮ ሌሎች ልኡካንን ወደ ስፍራው ትልካለች።

ላለፈው አንድ ወር በዝግጅት ላይ የቆየው የኢትዮጵያ ቡድን ወደ ውድድሩ ስፍራ ከማምራቱ አስቀድሞም ባለፈው ቅዳሜ በስካይ ላይት ሆቴል የሽኝትና የሰንደቅ



በዓለም ቻምፒዮና የሚሳተፈው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ብሄራዊ ቡድን ደማቅ የሽኝት መርሃ ግብር ተደርጎለት ወደ ውድድሩ ስፍራ አቅንቷል፤

አላማ ርክክብ መርሃ ግብር አካሂዷል። የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ቀጄላ መርዳሳ፣ የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታው አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ የአትሌቲክስ ስፖርት ሙያ ማህበራት እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችም በመርሃግብሩ ተገኝተዋል። ለአትሌቶቹ፣ ለአሰልጣኞችና ለቡድኑ አመራሮችም የአገር አደራ ምልክት የሚሆን የሰንደቅ አላማ ርክክብ ተደርጓል። በወቅቱም የቡድኑ አባላት የአገራቸውን ስም ለማስጠራት የሚያስችል ዝግጅት ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

በብሄራዊ ቡድኑ የረጅም ርቀት አሰልጣኝ ኮማንደር ሁሴን ሽቦ፤ አሰልጣኞችን በመወከል ለውድድሩ በቂ ዝግጅት ሲያደርጉ መቆየታቸውን ጠቁመዋል። አትሌቶችን በአካልም ሆነ በአእምሮ የተዘጋጁ በመሆኑ በዚያው ልክ አገራቸውን ለማስጠራት የሚችል ውጤት ያስመዘግባሉ የሚል ተስፋቸውንም አንጸባርቀዋል። የ3ሺ ሜትር መሰናክል ተወዳዳሪዋ አትሌት የወርቅውሃ ጌታቸው እንዲሁም የ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ተሳታፊው አትሌት ሰለሞን ባረጋም በተመሳሳይ ንግግር አድርገዋል። አትሌቶች ለዚህ ውድድር የሚመጥን ዝግጅት ሲያደርጉ መቆየታቸውን ጠቁመውም የአገራቸውን ባንዲራና ስም በድል ለማስጠራት በውድድሩ እንደሚካፈሉም ገልጸዋል።

በውድድሩ ላይ ቡድኑን በምክትልነት የሚመራው ኮማንደር አትሌት ማርቆስ ገነቲ፤ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ሲነሳ የሚታወሰው የኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ድል መሆኑን ጠቁሟል። በዚህ ውድድርም በተመሳሳይ ቡድኑ የአገሩን ስም ለማስጠራት የሚካፈል መሆኑን ገልጻል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ በበኩሏ፣ ይህ የውድድር መድረክ እርስ በእርስ በመረዳዳት በቡድን ስራና በኢትዮጵያዊነት መንፈስ በታሪክ መዝገብ ላይ የአገርን ስም ለማጻፍ የሚቻልበት ወርቃማ እድል መሆኑን ገልጻለች። በቻምፒዮናው ላይ የኢትዮጵያን ስም ለማስጠራት በትጋት ሲዘጋጁ የቆዩ አትሌቶችን፣ አሰልጣኞችና መላው ልኡካን ቡድን የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ታላቅነት በማንሳትም ቡድኑን አበረታታለች።

የሰንደቅ አላማ ርክክቡን ያደረጉት የኢፌዴሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስትሩ ቀጄላ መርዳሳ፤ ልኡካኑ የሄዱበትን ዓላማ ለማሳካት መንፈሰ ጠንካራ መሆን እንደሚገባቸው አሳስበዋል። ስፖርታዊ ውድድር ከአካላዊ ብቃት ባለፈ በአእምሮም ዝግጁ መሆንን ስለሚፈልግ መጠንከር ያስፈለጋል። በተለይ በቡድን መስራት እና ስፖርታዊ ስነምግባርን ማክበር ለአትሌቶች አስፈላጊ ነው። የቡድን መሪዎችም በአግባቡ ቡድኑን እንዲመሩና ለስኬት እንዲያበቁም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በአትሌቲክስ ስፖርት ስኬቷ የምትታወቀው ኢትዮጵያ በዚህ ውድድር ለ17ኛ ጊዜ የምትሳተፍ ሲሆን፤ ከአንድ ጊዜ ውጪ በሜዳሊያ ሰንጠረዡ መልካም የሚባል ውጤት አላት። በዚህም 29የወርቅ፣ 30የብር እና 26የነሃስ በድምሩ 85 ሜዳሊያዎችን በማግኘት በዓለም የደረጃ ሰንጠረዡ ሰባተኛ ላይ ልትቀመጥ ችላለች።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)

### ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር

በየሳምንቱ የሚታተም

## የድንች ምርትን ‹‹ብራንድ›› የማድረግ ጅማሮ

በጫልቱ ታምሩ

ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት ከማምረት ብቃት በዘለለ በብራንዲንግ ላይ የተመሰረተ እየሆነ መጥቷል። በዚህ አግባብ ብራንዲንግ ከመወዳደሪያ አቅም መለኪያዎች ውስጥ አንዱ ሊሆን ችሏል። ብዙዎቹ የቢዝነስ ተቋማት በአዳዲስ ምርታቸውና አገልግሎታቸው የብራንድ እሴትን እየተጠቀሙ ያለውም ለዚህ ነው። የውድድር ዘመን በተገቢው ሁኔታ የተዘጋጀ የብራንድ ስትራቴጂ በቢዝነስ ሥራ ከተወዳዳሪዎች ልቆ ለመገኘት ያግዛል።

በአለም ላይ ከሚመረቱ የግብርና ምርቶች ውስጥ ከስንዴ፣ በቆሎና ሩዝ በመቀጠል ድንች በአራተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠ ሲሆን በአገራችን ስትራተጂክ የግብርና ምርቶች ተብለው ከተለዩት መካከልም አንዱ ነው። በንጥረ ነገር ይዘቱ እንደሚባለው ሀይል ሰጪ ብቻ ሳይሆን ከከብት ወተት ጋር እና ከእንቁላል ጋር ተመጣጣኝ የሆነ 70 በመቶ ፕሮቲንና የተለያዩ ቫይታሚንና ሚኒራሎችን የያዘ ነው።

በሀገራችን ድንች በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብና ትግራይ ክልል በስፋት የሚመረት ሲሆን ምርቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደመጣ የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ። ከፍተኛ የድንች ምርት ከሚመረትባቸው አካባቢዎች ዋነኛው በሆነው በአማራ ክልል በ2012 ዓ.ም ከአምስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ በ2013 ዓ.ም ደግሞ ወደ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ተመርቷል።

የድንች ምርት በአማራ ክልል በሰሜንና ደቡብ ጎንደር በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም እንዲሁም በአዊ ዞን በስፋት ይመረታል። ምስራቅ ጎጃምና አዊ ዞን ዋና የድንች ምርት አብቃይ ናቸው። በአማራ ክልል በአዊ ዞን ከሚመረቱ የስራ ስር ምርቶች አትክልት ከ80 በመቶ በላይ የሚሸፈን ሲሆን በ2013 ዓ.ም በክልሉ ከተሸፈነው 33ሺ 883 ነጥብ አራት ሄክታር የድንች ምርት ውስጥ 10ሺ 332 ሄክታሩ የተሸፈነው በአዊ ዞን ነው። ክልሉ በዓመቱ ካመረተው አምስት ሚሊዮን 922 ሺ 291 ኩንታል ምርት ውስጥ አንድ ሚሊዮን 717 ሺ 462 ነጥብ አምስት ኩንታል የተሰበሰበው በዚሁ በአዊ ዞን ነው።

የድንች ምርት በአዊ ዞን በዓመት ሦስት ጊዜ የሚመረት ሲሆን መስከረም አጋማሽ ፣ የካቲት መጀመሪያና ግንቦት መጀመሪያ ምርት ተሰብስቦ ለገበያ የሚቀርቡበት ወቅት ነው። ከሁሉም የምርት ዘመናት ደግሞ የግንቦት ወር ከፍተኛ ምርት የሚገኝበት ነው። ምርቱ አጭር የሰብል ዘመን ያለው በመሆኑ ማሳን ለቀጣይ ሰብል ዝግጁ ለማድረግና ምርታማነት ለማሳደግም ይረዳል።

የአዊ ዞን አግሮ ኢኮሎጂ ድንችን ለማምረት እጅግ ተስማሚ ነው። የክልሉ ግብርና መረጃ እንደሚያሳየው በምርምር 400 ኩንታል እና በአርሶ አደር መሬት ደግሞ ከ300 ኩንታል በላይ በቃርዳ ይመረታል። አንዳንድ የድንች ዝርያዎች ለምሳሌ ‹‹በለጠ›› የሚባለው ዝርያ በምርምር በሄክታር 580 እንዲሁም በገበሬ ማሳ ደግሞ 400 ኩንታል እንደተመዘገበ የክልሉ ምርምር ማዕከል መረጃ ያሳያል።

ይህ ምርታማነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የመጣ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት በአማካይ በሄክታር 200 ኩንታል እንደሚመረት ባለሙያዎችና አርሶ አደሮች ያስረዳሉ። ይህ የሆነበት ምክንያትም በአካባቢው ያሉ የድንች ዝርያዎች ጊዜያቸው ያለፈባቸውና ለብዙ ዓመት አርሶ አደሩ ሲጠቀምባቸው የቆዩ በመሆናቸው ነው። ስለሆነም በምርምር በኩል አዳዲስ የተሻሻሉ ዝርያዎችን ለአርሶ አደሩ ማቅረብ እና ኅብረት ሥራ ማኅበራቱም ሆነ ግለሰቦች የዘር ብዜት ውስጥ መግባት እንዳለባቸው የዘርፉ የምርምር ባለሙያዎች ያስረዳሉ።

ከዚህ በተጨማሪ አርሶ አደሩ ለድንች ምርታማነት የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ማዳበሪያን በጥምር የሚጠቀም ቢሆንም የሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ዋጋ መናርና በወቅቱ ተደራሽ አለመሆን እየተፈታተነው ይገኛል።

በክልሉ በኅብረት ሥራ ማኅበራት ተደራጅተው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የሚያቀርቡ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በርካቶች ናቸው ። የዘንገና የመስኖ ልማት ኅብረት ሥራ ዩኒየን ድንች በማምረት ለገበያ ከሚያቀርቡት ውስጥ አንዱ ነው። ዩኒየኑ በ29 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በስምንት ሺ 175 አባል የአርሶ አደር መሬት ላይ ድንችን በማልማት ባለፉት ሦስት ዓመታት በየዓመቱ በአማካይ 10ሺ 750 ኩንታል ለገበያ አቅርቧል።

ዩንየኑ ከመሠረታዊ ኅብረት ማኅበራት ትላልቅና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የድንች ምርት ብቻ በመሰብሰብ በዋናነት በአካባቢው ላሉ ዩኒቨርሲቲዎችና ማረሚያ ቤቶች ያቀርባል። ይህ ደግሞ አባል አርሶ አደሩ ከሚያመርተው ምርት አንጻር ሲታይ እጅግ በጣም አናሳ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት በአካባቢው ካለው የቆየ የድንች ዝርያ አንጻር የሚመረተው ድንች በመጠን ደቃቅ በመሆኑ በገበያ ተፈላጊ እንዳይሆን አድርጎታል።

በመሆኑም አርሶ አደሩ በአብዛኛው ያመረተውን ምርት ዩንየኑ ስለማይረከበው በቀጥታ ለአካባቢ ነጋዴ በርካሽ ዋጋ ለማቅረብ ተገዷል። በዚህም አርሶ አደሩ በማሳ አልያም ደግሞ በኩንታል ‹‹አይተሽ ገምቺ›› በሚል አሰራር አንድ ኩንታል ማዳበሪያ ለነጋዴው ከ400 እስከ 450 ብር በማስረከብ ተጠቃሚው ዘንድ እስኪደርስ ዋጋው እስከ 900 ብር እንደሚደርስ ለመረዳት ተችሏል።

ድንች በአዊ ዞን አካባቢ ብዙ ጥቀም የሚሰጥ ነው። አርሶ አደሩ ድንችን እንደ እንጀራ በመሠረታዊ ምግብነት ይጠቀመዋል። እንዲሁም በቅቅል፣ በጥብስ /ቺፕስ/፣ በሉብሉብ ጥብስ፣ በወጥነት የሚጠቀመው ሲሆን በገበሬ ሰርቶ ማሳያና በምርምር ማእከል ደግሞ በእንጀራና በገንፎ መልክ መጠቀም እንደሚቻል ማስረጃዎች ያሳያሉ።

የአካባቢው ኅብረተሰብ ድንችን እንደ መሠረታዊ ምግብነት የሚጠቀመው በመሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች አርሶ አደሩ ምርታማ እንዲሆንና ያሉበትን የተለያዩ ችግሮች በመለየት ድጋፍ እየሰጡ ይገኛሉ።

ወርልድ ቪዥን በአዊ ዞን በባንጃ ወረዳ በስድስት ቀበሌዎች ላሉ አርሶ አደሮች ስልጠና በመስጠት፣ የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብና ለድንች ምርት ማቆያ የሚሆን መጋዘን በመገንባት ድጋፍ ያደርጋል። ከዚህም ሌላ የክልሉ ግብርና ማዕከል አርሶ አደሩ የተለያዩ የተሻሻሉ ዝርያዎችን እንዲጠቀም ስልጠና በመስጠት ድጋፍ ይሰጣል። ያም ሆኖ በድንች አመራረት ዙሪያ ለአርሶ አደሩ የሚሰጠው ስልጠና አናሳ መሆንና በልማቱ የሚደረገው እገዛ ውስንነት ያለበት በመሆኑ አካባቢው በድንች ምርት ያለውን ዕምቅ አቅም አሟጦ መጠቀም አልቻለም።

በአጠቃላይ የድንች ምርታማነትን አለማሳደግ፣ የምርት ማቆያ መጋዘንና ማጓጓዣ ችግር፣ የመሸጫ ቦታ ችግር፣ የፋይናንስ አቅም ውስንነት፣ የቴክኒክ ድጋፍ አናሳ መሆንና የገበያ ችግር አርሶ አደሩ የምርቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን አድርጎታል።

አንድን ምርት ብራንድ ማድረግ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት። ከነዚህ መካከልም ምርቱ በልዩ ምልክቱ አማካኝነት በቀላሉ እንዲለይ ያደርጋል፤ ምርት በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን፣ የደንበኛ ተዓማኒነትን ከመፍጠሩም ባሻገር የምርት ጥራት ደረጃን ያሻሽላል። በአጠቃላይ የድንች ብራንድ መደረግ ለአምራቹም ሆነ ተጠቃሚው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንደሚያመጣ ይጠበቃል።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ